# እውነት

ቁጥር 24

በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው
ዮሐ.17፡17

ጥር 2005 ዓ.ም.

## ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ? የሐ.ሥ.2፡37-42

**ክፍል - 1**

«ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» የሚለውን ይህን ጥያቄ ለጴጥሮስና ለሌሎች ሐዋርያት ያቀረቡት መንፈስ ቅዱስ በወረደበትና ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት በበዓለ ሃምሳ ዕለት ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ጌትነትና ክርስቶስነት በሰበከው ቃል ልባቸው የተነካ የእስራኤል ሰዎች ናቸው:: ይህ በዓለ ሃምሳ የተባለው ቀን እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጣቸው ሰባት በዓላት መካከል አራተኛው በዓል እንደሆነ ይታወቃል /ዘሌ.23፡15/፤ ይህም በዓል እስራኤል ሁሉ ከያሉበት ስፍራ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደ መረጠው ስፍራ ተሰብስበው በአንድነት ከሚያከብሯቸው ሦስት በዓላት አንዱ በዓል ነው/ዘዳ.16፡16/፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞተ ከተነሣና ካረገ በኋላ በተከበረው በዚህ በዓለ ሃምሳ ላይ ከሰማይ በታች ካሉ ሕዝብ በጸሎት የተጉ አይሁድ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራባት ዘንድ ወደ መረጣት ወደ ኢየሩሳሌም /2ዜና.6፡6/ መጥተው ነበር፤ ቢያንስ በዚያን ጊዜ ከታወቀው ዓለም ማለትም በእስያ፣ በአፍሪካና በአውሮፓ አህጉራት ከሚገኙ 15 አገሮች የመጡ አይሁድ እንደነበሩ ልንገነዘብ እንችላለን/የሐ.ሥ.2፡9-11/:: ኢየሩሳሌም ከወትሮው ይልቅ በብዙ ሺህ ሕዝብ የምትጨናነቅበትና በተለይም በዓሉ የሚከበርበት ቤተመቅደስ በብዙ ያሸበረቀ ሥርዓት የሚደምቅበት ጊዜ እንደሚሆን ማሰብ ይቻላል፤ ይሁንና እግዚአብሔርን በብዙ ለማክበር የተሰበሰበው የእስራኤል ሕዝብ በሥጋ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ልጅ ያልተቀበለና ከሃምሳ ቀን በፊት ከሰፈሩ ውጭ አውጥቶ የሰቀለ ሕዝብ ነበር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሞተው፣ ከሙታን ከተነሳውና በእግዚአብሔር ቀኝ ካለው ጋር የተባበሩት 120 ደቀመዛሙርት በሚኖሩበት ሰገነት ውስጥ በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር፤ ታዲያ በዕለቱ መንፈስ ቅዱስ የወረደውም ለእነርሱ ነበር እንጂ በቤተመቅደስ በዓሉን ለሚያከብሩት አልነበረም፤ በዚህም እግዚአብሔር

*(ወደ ገጽ 4 ይዞራል)*

## ስለክርስቶስ አገልጋዮች መናገር ያለብን እንዴት ነው?

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉ የሆነች ቤተክርስቲያኑን ለማነጽ ልዩ ልዩ ጸጋ የሰጣቸውን አገልጋዮች ለሰዎች መስጠቱ ይታወቃል:: እነዚህም አገልጋዮች እንደእኛው የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ በብርታትም ሆነ በድካም የሚያልፉበት ሁኔታ አለ:: ታዲያ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለእነዚህ የክርስቶስ አገልጋዮች መናገር ያለብን እንዴት እንደሆነ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር እናነባለን:: ጽሑፉ የተወሰደው እ.ኤ.አ. በ1881 ከታተመ «ዘባይብል ሄራልድ» ከተባለ ጎትመት ውስጥ ነው:: ጸሐፊው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ባደረጉት የደብዳቤ ልውውጥ ውስጥ ያስፈሩት ምክር ሲሆን ለዘመናችን አንባቢያንም ጠቀሜታው የጎላ ሆኖ ስለታየን በዚህ እትም ላይ ተርጉመን አቅርበንዋል::

«በፍጥነት ደግሜ የምጽፍልህ ክፉ ንግግርን በተመለከተ አንተ ካልከው ጋር የምስማማ በመሆኔ ነው:: በሐሰት ወሬዎች የመጡ የሚያስለቅሱ አጋጣሚዎች እና ጎጂ የሆኑ ስም ማጥፋቶች በእኔ ፊት ቀርበዋል:: እነዚህ ነገሮች በፍጥነት ተቀባይነት እንዲያገኙና እንዲሰራጩ ያለው ዝግጁነት የሚያስነባ በደል እንደሆነና ንስሐ ካልገባንም በቀር ጌታ ጣልቃ ገብቶ እንዲፈርድ የሚገደድበት እንደሆነ በእውነት አምናለሁ፤ ላለፉት ረጅም ጊዜያት ራሴው ካላረጋገጥሁ በቀር አንድን ወሬ አላምንም ነበር:: /ዘጸ.23፡1 ይህንን ኃላፊነት ይጥልብናል::/»

ከውስጡ የተወሰደውን ይህንን መልእክት ለያዘው ደብዳቤ

(*ወደ ገጽ 5 ይዞራል*)

### በውስጥ ገጾች

◆ ከእርሱ ጋር በክብር እንገለጣለን ........ 2
◆ የፈርኦን ልብ ........ 2
◆ ጉበኛው ........ 3
◆ የጌዴዎን እምነት ........ 9
◆ ጊዜና ዘላለም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ........ 10
◆ አንዳንዶች ለምን የእግዚአብሔርን መኖር ይክዳሉ? ........ 13
◆ መዝሙሩና እረኛው ........ 13
◆ የጥያቄዎቻችሁ መልሶች........ 14
◆ በረከተ ጥበብ ........ 15
◆ የእግዚአብሔር በግ ........ 16

እውነት ቅጽ 6 ቁጥር 24

# እውነት

ዋና አዘጋጅ - ጸጋዬ ትእዛዙ
ም/ዋና አዘጋጅ - ኃይሉ መስፍን

## መልእክተ እውነት

### ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ

**«እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፡፡ ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፡፡ ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ»**

**(ቈላ.3፡1-4)**

ይህ እጅግ የተወደደና በጣም ታዋቂ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አማኞች በክርስቶስ በማመናቸው የተነሳ ከእርሱ ጋር የያዙትን ስፍራ የሚያሳይ ነው፡፡ እርሱ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቷል፤ አማኞችም ከእርሱ ጋር ያላቸው ታሪክ የሚጀምረው ከዚህ የቀራንዮው የመስቀል ላይ ሞቱ ነው፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያ ያመኑት የተሰቀለው ክርሰቶስ ተሰብኮላቸው ሲሆን በኋላ በውኃ ጥምቀት እንደመሰከሩትም፣ ባመኑ ጊዜ ከሞቱ ጋር አንድ ሆነዋል /1ቆሮ1፡23፤ ሮሜ6፡3/፡፡

ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ቢሞትም «ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለም»/የሐ.ሥ.2፡24/፡፡ እኛን ስለማጽደቅ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሳ /ሮሜ4፡25፤ 1ቆሮ.15፡4/፤ ተነስቶም ደቀመዛሙርቱ እያዩት ወደ ሰማይ ወደ አባቱ ሲያርግ ደመና ከዐይናቸው ሰውራ ተቀበለችው /የሐ.ሥ.1፡9/፡፡ አሁን ከሁሉ በላይ ሆኖ በዚያ በሰማያዊ ስፍራ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ /1ጴጥ.3፡22/፤ አማኞችም አሁን በአካለ ሥጋ በምድር ቢሆኑም እግዚአብሔር ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከክርስቶስ ጋር ያስነሳቸውና በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር ያስቀመጣቸው/የሰወራቸው/ ሰዎች ናቸው /ኤፌ2፡6/፡፡

ከዚህም በላይ ጌታ ኢየሱስ አንድ ቀን የእርሱ የሆኑትን ሊወስድ እስከ አየር ሲመጣ ያን ጊዜ እርሱን ለመቀበል በደመና ይነጠቃሉ/1ተሰ.4፡17/፡፡ ከዚህች ከንቱ ዓለምም በአካል ተለይተው እርሱ ባለበት በሰማያዊ ስፍራ ይሰወራሉ፡፡ ከዚያም እርሱ በሥጋ በተገለጠ ጊዜ እንደነበረው በውርደት ሳይሆን በክብር የሚገለጥበት ጊዜ ይመጣል፡፡ በራእ.19፡11-14 እንደተነገረው በሰማይ ያሉት ጭፍራዎች ማለትም የተሰወሩት አማኞች እርሱን መስለው ከተከፈተው ሰማይ ይወጣሉ፤ እርሱ ይፈርድና ይነግሥ ዘንድ ከዚያ ከተሰወረበት ሰማይ በሚገለጥበትና ዓይን ሁሉ የወጉትም እርሱን በሚያዩበት/ራእ1፡7/ በዚያ ጊዜ አማኞችም ከእርሱ ጋር በክብር ይገለጣሉ፡፡

# የፈርዖን ልብ

እግዚአብሔር እጅግ ትዕቢተኛ የተባለውን ልብ ሊያደቅ ኵራተኛንም መንፈስ ከትቢያ ላይ ሊጥል ይቻለዋል፤ «በትዕቢት የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና» /ዳን4፡37/፡፡ ሰው ለራሱ አንዳች ግምት በመስጠት ራሱ የራሱ ጌታ የሆነ ይመስል ራሱን በከንቱ ውዳሴ ከፍ በማድረግ በኵራት ይመላለስ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ስለእውነተኛ ማንነቱና ጠባዩ እንደዚሁም ከንቱነቱ የሚያውቀው ምንኛ ጥቂቱን ነው! በክፉ ጥረቱ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማደናቀፍ ሰይጣን በእጁ ውስጥ የያዘውና የሚጠቀምበት መሳሪያ እንደሆነ አያስተውልም፡፡ እጅግ ድንቅ የሆነ የማሰብ ችሎታ፣ እጅግ በጣም አመቺ የሆነ ብልህነት፣ በቀላሉ የማይሸነፍ ጉልበት አለን የሚሉ የሰው ልጆች በቀጥታ በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር ካልዋሉ ሰይጣን የጨለማ ዕቅዶቹን የሚፈጽምባቸው በእጁ ያሉ መሳሪያዎቹ ያደርጋቸዋል፡፡ የራሱ ጌታ የሆነ ሰው የለም፤ ወይ የሰይጣን ተገዥ ነው፤ አልያም የክርስቶስ ተገዥ ነው፡፡ የግብጽ ንጉሥ ነጻ ሰው ነኝ ሊል ይችላል፤ ነገር ግን በሌላው እጅ ውስጥ ያለ መሳሪያ እንደሆነ አላስተዋለም፡፡ ከዙፋኑ በስተጀርባ ሰይጣን ነበር፡፡ ፈርዖን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቃወም ራሱን ያዘጋጀ ሰው ስለነበር ልቡ ይደነድንና ይታወር ዘንድ ራሱ ፈቅዶ በመረጠው ጌታው እጅ ተላልፎ ተሰጠ፡፡

ይህም «እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አደነደነ» ተብሎ በተደጋጋሚ የምናገኘውን አባባል ያብራራልናል፡፡ የዚህን ከባድ ዓረፍተ ነገር ሙሉና ግልጥ የሆነ ስሜት ወደጎን ለመተው መሞከሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ሰው የእግዚአ ብሔርን የምስክር ብርሃን የሚቃወምና ለመቀበል የማይፈልግ ከሆነ ልቡ እንዲታወርና እንዲደነድን ተላልፎ ይሰጣል፡፡ ብርሃንን አልቀበልም ሲል የፈለገው ጨለማውን ነውና ለጨለማ ይተዋል ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ያን ሰው ለራሱ ለሰውየው ማንነት ሲተወው ሰይጣን ይቆጣጠረውና ወደ ዘላለማዊ ጥፋት አሽቀንጥሮ ቁልቁል እስኪወረውረው ድረስ ይጠቀምበታል፡፡ እግዚአብሔር ልቀቅ ብሎ ያዘዘውን ይዞ ለማስቀረት የጣረው ጥረት እጅግ ታላቅ ሞኝነት መሆኑን ያይ ዘንድ ለፈርዖን ከልክ በላይ የሆነ ብርሃን በርቶለት ነበር፡፡ ሆኖም እውነተኛው የልቡ ፈቃድ እግዚአብሔርን መቃወም በመሆኑ «በምድር ሁሉ» የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ዕቃ እስኪሆን ድረስ ተተወ፡፡ እግዚአብሔርን ለመቃወም የሚፈልጉ ሁሉ ሳይቸገሩ እዚህ ውስጥ ይገባሉ፤ ትርፋቸውም ነፍሳቸውን ማጥፋት ነው፡፡

«ስለዚህም ምክንያት በእውነት

*(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)*

# ጉበኛው


በመጽሐፍ ቅዱስ ጉበኛ የሚለው ቃል በተለያዩ ቦታዎች የተጻፈ ቢሆንም የአሁኑ የጽሑፋችን ትኩረት በሕዝ.33፡1-9 ያለው ይሆናል:: ይህም ቀጥሎ ይነበባል::

«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ የሰው ልጅ ሆይ ለሕዝብህ ልጆች ተናገር፤ እንዲህም በላቸው፣ ሰይፍን በምድር ላይ ባመጣሁ ጊዜ የምድር ሕዝብ ከመካከላቸው ሰውን ወስደው ለራሳቸው ጉበኛ ቢያደርጉ እርሱም በምድር ላይ የመጣውን ሰይፍ ባየ ጊዜ መለከትን ቢነፋ ሕዝብንም ቢያስጠነቅቅ የመለከትን ድምፅ የሚሰማ ሰው ባይጠነቀቅ ሰይፍ መጥቶ ቢወስደው ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል:: የመለከቱን ድምፅ ሰምቶ ስላልተጠነቀቀ ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል:: ቢጠነቀቅስ ኖሮ ነፍሱን ባዳነ ነበር:: ጉበኛው ግን ሰይፍ ሲመጣ ቢያይ መለከቱንም ባይነፋ ሕዝቡንም ባያስጠነቅቅ ሰይፍም መጥቶ አንድ ሰው ከእነርሱ ቢወስድ እርሱ በኃጢአቱ ተወስዷል፤ ደሙን ግን ከጉበኛው እጅ እፈልጋለሁ::

አንተም የሰው ልጅ ሆይ ለእስራኤል ቤት ጉበኛ አድርጌሃለሁ፤ ከአፌ ቃሌን ስማ፤ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው:: ኃጢአተኛውን ኃጢአተኛ ሆይ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁ ጊዜ ኃጢአተኛውን ከመንገዱ ታስጠነቅቅ ዘንድ ባትናገር ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ:: ነገር ግን ከመንገዱ ይመለስ ዘንድ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቀው፣ እርሱም ከመንገዱ ባይመለስ በኃጢአቱ ይሞታል አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል::» ይላል::

«ጉበኛ» የእንግሊዘኛ አቻ ትርጉሙ «Watchman» የሚለው ሲሆን በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ «Watchman» የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በተለያዩ ትርጉም ተቀምጧል:: ለምሳሌ/1ሳሙ.18፡24/ በሀገር ቅጥር ላይ ያለ አካባቢውን የሚቆጣጠር «ዘበኛ»፣ በ2ነገ.9፡17 «ሰላዩ»፣ በሆሴ.1፡8 «ጠባቂው» ተብሏል:: በዚህ በሕዝ.33 ደግሞ «ጉበኛ» በማለት አስቀምጦታል:: የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ልዩነት ቢኖርበትም በእንግሊዝኛው ግን በተመሳሳይ ቃል ይነበባል:: ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለሕዝቡ የሚሰጥ «ጠባቂ»፣ አሊያም በዘመናችን እንዳሉ የአገርን ደህንነት ለመጠበቅ በስለላ ዘርፍ የተሰማሩትን ይመስላል:: ተግባሩም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ችግሩን ማሳየትና ማስጠንቀቅ ይሆናል::

በ1ሳሙ.14፡16 በብንያም ጊልቦአ ያሉ የሳኦል ዘበኞች ተመለከቱ «እነሆም ሠራዊቱ ወዲህና ወዲያ እየተራወጡ ተበታተኑ:: ሳኦልም ከእነርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ እስኪ ተቋጠሩ ከእኛ ዘንድ የሄደ ማን እንደሆነ ተመልከቱ አላቸው» ይላል:: ጠባቂው ለሳኦል በፍልስጥኤም ሰፈር ወጊያ እንዳለና ከፍልስጥኤም ጋር እየተዋጉ ያሉት ዮናታንና ጋሻ ጃግሬው እንደሆኑ ነበር የነገረው:: በ2ሳሙ.18፡24 «ዘበኛውም በቅጥሩ ላይ ... ዓይኑን አቅንቶ ብቻውን የሚሮጥ ሰው አየ፤ አኪማአስ የንጉስ ጠላቶች የሆኑት የነአቤሴሎምን መሞት ለመንገር ወደ ንጉሡ ሲሮጥ ገና ከሩቅ ሳለ ጉበኛው በንቃት ይከታተለው ነበር፤ በመጠበቂያው ላይ ሆኖ በትጋት በመጠበቅ ከሰፈሩ ውጪ የሚሆነውን ሁሉ ይቆጣጠር ነበር» ይላል:: በ2ነገ.9፡17 በኢይዝራኤልም ግንብ ላይ የቆመው «ሰላይ»/ጉበኛ/ ከሩቅ የሚመጣውን አትኩሮ ስለተመለከተ «ጭፍራ አያለሁ» አለ:: ይህ ጉበኛ/ሰላይ/ ለንጉሡ ለኢዮራም ከሩቅ የሚመጣ ጭፍራ ሲመለከት ቀድሞ ጌታውን አስጠነቀቀው የሚመጣው ኢዩ ሲሆን የአክዓብን ቤት ለመበቀል ነበር፤ ቢሆንም ኢዩና ሠራዊቱ ከጠባቂው ዓይን ግን አልራቁም ነበር:: ጠባቂዎቹ ማስጠንቀቂያቸውን በጊዜው እየተከታተሉ ያደርሱ እንደነበር አስተውለናል:: የጉበኛው ዋነኛ ሥራ ከተማን መጠበቅ እና ከከተማው ውጪ ሕዝቡን፣ መንግስቱን፣




Encarta Encyclopedia, Bernard Boutrit/Woodfin Camp and Associates, Inc.

ከተማዋን ሊጐዳ የመጣ ማንኛውንም ባላንጣ ለንጉሥ /ለሕዝቡ/ መግለጥና ከዚያ ከሚመጣ አደጋ እንዲጠበቅ ማድረግ ነበር:: ይህ «ጉበኛ» ያለ እንቅልፍ በንቃት ለሕዝቡና ለሃገር ጥቅም የሚሠራ ነው:: የጉበኛው መዘናጋት ከተማንና ሕዝብን ያጠፋልና በፍጹም ንቃት ሊጠብቅ ይጠበቅበት ነበር::

በሕዝ.33፡1-20 ያለው መልዕክት የሚያመለክተን ይህንኑ ነው:: ሰልፍ በመጣ ጊዜ ለሕዝቡ ቀንደ መለከትን በመንፋት ሕዝቡን ለጦርነትና ለመከላከል ማዘጋጀት ይኖርበታል፤ አለዚያ ይህንን ባያደርግ ግን በሚደርሰው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል ሕይወቱንም ጭምር ያስከፍለዋል:: እርሱ ግን ቀንደ መለከቱን ቢነፋና ሕዝቡ ቢዘናጋ ደሙ በሕዝቡ ላይ ይሆናል፤ ስለዚህ የጉበኛው ሥራ ማየትና ማስጠንቀቅ ነው:: ጉበኛው ግን ሰይፍ ሲመጣ ቢያይ፣ መለከቱን ባይነፋ፣ ሕዝቡንም ባያስጠነቅቅ ሰይፍም መጥቶ አንድ ሰው ከእነርሱ ቢወስድ እርሱ በኃጢአቱ ተወስዷል ደሙ ግን ከጉበኛው እጅ ይፈልጋል::

ጉበኛው ለዚያች ሃገር ወይም ከተማ አይን ሆኖ ያገለግላል፤ በዙሪያው ያለውን እንቅስቃሴ ይመለከታል:: በቀደሙት ክፍሎች እንዳየነው ጉበኞች ለሳኦል፣ ለዳዊት፣ ለኢዮራም... ከውጪ ያለውን ተመልክተው ሲያሳውቋቸው አይተናል::

እንግዲህ «ከጉበኛው የሚጠበቀው» ያየውን ያስተዋለውን ማሳወቅ ነው፤ ሰልፍን የመከላከል፣ ከተማውን ለማጥቃትና ለማርከስ የሚመጣውን ጠላት መከላከል የሕዝቡ ፊንታ ነው:: ጠንቃቃ ያልሆነ ጉበኛ ያለው ሀገር የከበበውን አያውቅም፤ በማንኛውም ወቅት በጠላት ቁጥጥር ሥር እንደሚሆን የታመነ ነው:: ለምሳሌ

*(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)*

## ወንድሞች ሆይ... ከገጽ 1 የዞረ

እስራኤልን ትቶ የኢየሱስ ክርስቶስ ለሆኑት የሰጠውን እውቅና አሳይቷል:: መንፈስ ቅዱስ በሰገነቱ ውስጥ በነበሩት ላይ በወረደ ጊዜ ሕዝቡን ወደዚያ ስፍራ የሰበሰበው ከሰማይ የመጣው ድምፅ ነበር፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሲገልጥ «ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው» /የሐ.ሥ.2፡1/ በማለት በዕለቱ የነበረውን ክስተት ከነገረን በኋላ «ይህ ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ» ይለናል /ቁ.6/፤ በመሆኑም የካህናት አለቆችም ሆኑ የሕዝብ ሽማግሌዎች ሊከላከሉት በማይችሉት መልኩ ለበዓሉ የመጣው ሕዝብ ድምፁ ወደተሰማበት በሰገነቱ ቤት ወደሚኖሩት ወደ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት መጣ፤ «እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ» /ቁ.6/:: አንዳንዶች አመነቱ ሌሎች ደግሞ አፌዙ /ቁ.12-13/:: ከዚያ በኋላ ጴጥሮስ ከአስራ አንዱ ጋር ቆሞ በቅድሚያ ከትንቢተ ኢዩኤል ቃሉን በመጥቀስ ያዩት ነገር የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ካሳያቸው በኋላ «የእስራኤል ሰዎች ሆይ ስሙ» /ቁ.22/ በማለት ስለ ክርስቶስ በሰፊው ሰበከላቸው፤ ጌታ አልፎ በተሰጠባት ምሽት በገረዶችና በሎሌዎች ፊት «አላውቀውም» ብሎ የነበረው ጴጥሮስ /ሉቃ.22፡54-61/ የበዓለ ሃምሳ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ ጊዜ በሙሉ ድፍረትና ሥልጣን ስለ ኢየሱስ መሰከረ፤ ከጌታ የተሰጡትን የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎች ተጠቅሞ ለብዙዎች በሩን መክፈት ጀመረ፤ በተለይ በዕለቱ በሰበከው ቃል ውስጥ ትኵረት የሰጠው ጉዳይ ስለ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ፣ እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ስለመቀመጡ ሲሆን ከመዝሙራት መጽሐፍ እየጠቀሰ ልብን በሚነካ መልኩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰብኮ ነበር:: በስብከቱ ማጠቃለያ ላይም «እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ» አላቸው /ቁ.36/:: ቀደም ሲል በክርስቶስ መገደል የተስማሙት እነዚህ የእስራኤል ሰዎች «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይተባበራል» ብለው ያስቡ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፤ ነገር ግን አሁን ያዩትና የሰሙት ነገር እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሳይሆን ከተሰቀለው ጋር መሆኑን የሚያሳይ ነበር፤ እነርሱ የሰቀሉትን ከሙታን አስነሥቶ በቀኙ በማስቀመጥ ጌታም ክርስቶስም አድርጎታልና፤ ስለሆነም በጴጥሮስ የተሰበከውን ይህን ቃል በሰሙ ጊዜም ልባቸው ተነካ፤ የሰሙት ቃል እነርሱ እንደተሳሳቱና ጥፋተኞች እንደሆኑ ለልባቸው ስላሳያቸው ልባቸው ሊነካ ቻለ፤ ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ለመስማማትና ከፍርድ ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት «ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» ብለው ለመጠየቅ ቻሉ::

ጌታ ይህን ጥያቄ የሚያነሱ ሰዎችን ዛሬም ይፈልጋል:: ሐዋርያት የሰበኩት ክርስቶስ ዛሬም በተለያየ መንገድ እርሱን ለማይከተሉት ሁሉ እየተሰበከ ነው:: እርሱ ስለኃጢአታችን መሞቱ ስለጽድቃችን መነሳቱ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ የአካሉ ራስ፣ የእግዚአብሔር ቤት ሊቀካህናት ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እየሠራ እንዳለ ዘወትር እየተነገረ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ስለክርስቶስ ማንነት በሚሰበከው በዚህ የወንጌል ቃል ልባቸውን የነካቸው ሰዎች አንድ ቀን የወንጌልን እውነት የመሰከሩላቸውን ሰዎች ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ? ብለው መጠየቃቸው አይቀርም፤ እነዚያ የእስራኤል ሰዎች እነ ጴጥሮስን ጥቂት ቀደም ብሎ «እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ <u>የገሊላ ሰዎች</u> አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበት የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?» ብለዋቸው ነበር፤ ይህም አነጋገር የንቀትና የማቃለል ነበር፤ ምክንያቱም ገሊላ በእነርሱ ዘንድ መልካም የሆነ ነገር ወይም ነቢይ ይገኝባታል ተብላ የማትታሰብ ቦታ እንደሆነች ከሌሎች ንባቦች እንረዳለን /ዮሐ.1፡47፤ 7፡52/:: አሁን ግን በሰሙት ቃል ልባቸው ሲነካ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት «ወንድሞች ሆይ» ብለው በመጥራት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመጠየቅ ቻሉ:: እነዚህ ሰዎች ቀደም ሲል የሚመኩበት የኦሪት ሥርዓት የነበራቸውና ከእነርሱ ውጭ እግዚአብሔር ለራሱ ሕዝብ ሊወስድ እንደሚችል የማያውቁና የማያስቡ ነበሩ፤ ልባቸው ሲነካ ግን ለወንጌል እውነት ተሸነፉ::

በኋላ ላይ በሐዋርያው በጳውሎስ ህይወት የሆነው ለውጥም እንዲሁ ነበር፤ እርሱ አስቀድሞ ስለ ሕጉ በመቅናት «ቤተክርስቲያንን ያፈርስ ነበር፤ ወደ ሁሉም ቤት በመግባት ወንዶችንም ሴቶችንም እየጎተተ ወደ ወኅኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር» /የሐ.ሥ.8፡1/፤ ይሁን እንጂ በደማስቆ መንገድ ላይ ጌታ ባገኘው ጊዜ እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ «ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?» ነበር ያለው፤ ዛሬም አፍኣዊ በሆነ ሥርዓት እግዚአብሔርን ያገለገሉ የሚመስላቸው ሰዎች በክርስቶስ ፍቅርና በወንጌል እውነት ሲሸነፉ «ጌታ ሆይ ምን እናድርግ?» የሚለውን ይህን ጥያቄ ሊጠይቁ ይገባል፤ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ በወንጌል የሚሰሙ ሁሉ ይህን ጥያቄ ቢጠይቁ ነፍሳቸውን የሚያሳርፍ ምላሽ ያገኛሉ::

ከአሕዛብ ወገን የነበረው የፊልጵስዩስ የወኅኒ ጠባቂም በወኅኒ ቤቱ ውስጥ ጌታ ባደረገው ነገር ልቡ ሲሸነፍ ያነሳው ጥያቄ ተመሳሳይ ነበር፤ ሐዋርያው ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ በመሰከሩት ወንጌል ምክንያት በብዙ ከተደበደቡ በኋላ ወደ ወኅኒ ሲጣሉ ትእዛዝ ተቀብሎ እግራቸውን ከግንድ ጋር አጣብቆ የጠረቃቸው ይህ የወኅኒ ቤት ጠባቂ ነበር፤ ሆኖም በመንፈቀ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ እግዚአብሔርን በዜማ ሲያመሰግኑ የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ የሆነውን ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥና የደጆቹን መከፈት እንዲሁም የሁሉም እስራት መፈታቱን ሲመለከት ጳውሎስና ሲላስን ወደ ውጭ አውጥቶ «ጌቶቼ ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» አላቸው/የሐ.ሥ.16፡19-30/::

ቀደም ሲል የወንጌል ሠራተኞችን እስከማሳደድና በእነርሱ ላይ መከራን እስከማምጣት የደረሱ ሰዎች አንድ ቀን በእግዚአብሔር አሠራር ልባቸውን የሚነካ ነገር በፊታቸው ሊፈጠር ይችላል:: ያን ጊዜ የተለያየ ትርጉም ከመስጠትና ከይሉኝታ ተቆጥበው ጊዜ ሳያጠፉ «እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል» ሊሉ እንደሚገባ ይህ ታሪክ ያስተምረናል:: በኢየሱስ መገደል ተስማምተው የነበሩት አይሁድም ሆኑ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ የነበረው ሳውል እንደዚሁም ይህ የወኅኒ ቤት ጠባቂ «ምን እናድርግ?» ለሚለው ጥያቄአቸው ምላሽ እንዳገኙ ዛሬም ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች ልብን የሚያሳርፍ መልስ አለ::

የበዓለ ሃምሳ ዕለት «ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» የሚለውን ጥያቄ ላቀረቡት ሰዎች የተሰጠው መልስም «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፤ የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና» የሚል ሲሆን በተጨማሪም «ከዚህ ጠማማ ትውልድ ዳኑ» ተብለው ተመክረዋል /የሐ.ሥ.2፡38-42/::

በቤተክርስቲያን ምስረታ ዕለት ለመጀመሪያዎቹ አማኞች የተሰጡ እነዚህ መልሶች ዛሬም ቢሆን በወንጌል ቃል ልባቸው የተነካ ሰዎች ከዚያ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትምህርትን የሚሰጡ በመሆናቸው እያንዳንዳቸውን ቀጥሎ እንመለከታቸዋለን::

ይቀጥላል

# ስለ ክርስቶስ አገልጋዮች ...

*ከገጽ 1 የዞረ*

የሚከተለው ምላሽ ተሰጥቶ ነበር:: ኅብረት የሚያድገው የሚያገለግሉ ወንድሞችን መልካም ስም በመጠበቅ ነው:: «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ የሚተጉ ብዙዎች እንዲኖሩ እመኛለሁ:: የሚያለግሉ ወንድሞች ሁሉ በፍቅር እንዲያስቡ፣ አንዱ ሌላውን በማድነቅ እንዲጽፉና እንዲናገሩ እና ጎጂ ከሆነው እኔነት በላይ መሆናቸውንና በጌታ ነገር አብዝቶ መያዛቸውን እንዲያሳዩ፣ የመንፈስ ቅዱስ ቃል እና ሥራው ለእርሱ ክብር የሚያውሉ እንዲሆኑ ከጌታና ከቅዱሳን ሐዋርያቱ ይማሩ ዘንድ ከልቤ በይበልጥ እመኛለሁ:: እኛ በዚህ ጉዳይ በሚያሳዝን ሁኔታ ጉድለት እንዳለብን እርግጠኛ ነኝ፤ አገልጋዩ በፊታችን የሚታየን እርሱ ሰው እንደመሆኑ ያለው ሰብእና ነው፤ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር በሰማይ ካከበረው እና ከተሳዳቢዎችና ከተቺዎች መልካም ስሙን ከጠበቀለት ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አገልጋዩ ካለው ግንኙነት አንጻር አናየውም:: ዓይኖቼን በአባቱ ዙፋን ላይ ወደተቀመ ጠው ወደ እግዚአብሔር ልጅ ሳደርግ አንድ ነገር አያለሁ፤ የእርሱን ስም ንጹሕ ለማድረግ ያለውን የእግዚአብሔርን ቁር ጠኛ ውሳኔ:: «ስለጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ነው» እንዳለ /ዮሐ.16:9/:: እንዲሁም የማስታረቅ አገልግሎት ሰማያዊ ልዑካን የሆኑት የእርሱ መልእክተኞች ለእርሱ እንዴት የቀረቡና የተወደዱ እንደሆኑ ስናውቅ በግልጽ የማይታይ የሐሰት ክስን በግል በእነርሱ ላይ በማንሳት የአገልግሎታቸው ውጤት ሲደናቀፍ እርሱን የሚያስቆጣው እንደሚሆን እንገነዘባለን:: የእርሱ አገልጋዮች ክብሩ እየሰፋ እንዲሄድ ሲሠሩ፣ የክርስቶስ በመሆናቸው ምክንያት አንዱ ለሌላው ግድ የሚላቸው ሲሆኑ የእርሱን ልብ ደስ ያሰኘዋል፤ ጠባያቸውን ለመቆጣጠር በሁሉም አጋጣሚዎች አብዝተው የሚጠ ነቀቁ ሐሜተኞችን፣ ወሬኞችንና ክፉ ተናጋሪዎችን የሚያሳፍሩ ሲሆኑ ደስ ይለዋል::

አንድ አገልጋይ ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ ከፍ ማለት በጣም አስረግጦ እየሰበከ ሳለ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ራሱን ከፍ በሚያደርግ ጊዜ በቅዱሳን መካከል በጣም ክፉ ተጽዕኖ ማሳደሩ ግድ ይሆናል:: እንደዚህ አይነት አገልጋዮች በግል ከቅዱሳን ጋር የሚያደርጉት ንግግር በመድረክ ሲያገለግሉ ከአፋቸው ቅዱሳን ከሰሚቸው፣ ከፍ ካሉ የክርስቲያን ነገሮች ጋር ሲቃረኑ፣ ይህ ሁኔታ አፍራሽ ውጤትን እንደሚያመጣ እርግጠኛ ነኝ:: ምክንያቱም ከፍ ያሉት ነገሮች በዝቅተኛዎቹ ነገሮች እንዲጠፉ ስለሚደረግ እና የአማኞች ኀሊናም የሚያገለግሏቸው ሰዎች በጣም ምድራዊ በሚሆኑ ጊዜ በሰማያዊ ነገሮች ላይ አንጻች እውነታ እንዳላቸውና እንደሌላቸው ጥያቄ ውስጥ ስለሚገቡ ነው፤ ይህ ካልሆነ ግን /ጥያቄው ካልተነሳ/ ይበልጡኑ የከፋ ነው:: ስለሰማያዊ ነገሮች በአደባባይ በሚሰበኩ ስብከቶች እና በግል ክፉና ሐሰተኛ ነገሮችን እያጸመጡና እያወሩ በመያዝ መካከል ያለ ሞራላዊ ልዩነት የክርስቶስን ክቡር ስም ለማክበርና የእርሱን አገልጋዮች መልካም ስም ለመጠበቅ ከፍ ያለ ስሜት ላላቸው ነፍሳት በጣም መሰናክል መሆኑ የማይቀር ነው::

ጌታ ስለ ራሱ አገልጋዮች የሚናገርበት መንገድ ስለመጥምቁ ዮሐንስ በተናገረው «እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ» /ዮሐ.5:35/፣ «ከነቢይ የሚበልጥ ... እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም» በሚለው የታወቀ ንግግሩ ውስጥ ይታያል/ማቴ.11:11/:: መጥምቁ ዮሐንስ ስለእውነተኛው ብርሃን ምስክር ሆኖ ነበር፤ አሁን ደግሞ ጌታ የእርሱ ምስክር ሆነ:: ጌታ በዚያ ጊዜ በእስር ላይ ለነበረው ለዚህ ታላቅ ሰባኪ በሕዝብ ፊት ከሴቶች ከተወለዱት መካከል የሚበልጥ እንደሆነ በደቀመዛሙርቱ አማካኝነት ማረጋገጫ ሰጥቶ መስክሮለታል:: ዮሐንስም «እርሱ ሊልቅ እኔ ላንስ ይገባል» በማለት ተናግሮ ነበር፤ ያ ብርሃን /ዮሐንስ/ በቀትር በሚያበራበት ወቅት ኢየሱስ ለሕዝቡ ዮሐንስን በተመለከተ /እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ/ በማለት መናገር ጀመረ:: እርሱ /ጌታ/ እየላቀ የሄደው ዮሐንስን እያስወገደ ሳይሆን የራሱ በሆነ ክብርና ከሰማይ፣ ከምድር ከሲኦልም ሳይቀር ስለ ድንቅ ሥራዎቹ በነበረው ምስክር ነው:: እርሱ ወድቆ የነበረውን ደቀመዝሙሩን ጴጥሮስን እስኪመልሰው እና በሰጠው ሥራ ሁሉ በእርሱ ላይ ያለውን አመኔታ በፊታቸው እስኪገልጥ ድረስ ዓለምን አልተወም/አላረገም/ ነበር፤ በበዓለ ሃምሳ ዕለትም የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎችን በገሃድ ሰጠው፤ አስከፊ በሆነ መልኩ ቢወድቅም በአስራ ሁለቱ መካካል በነበረው ቀዳሚ ስፍራ ጠበቀው:: በሚያሳዝን ሁኔታ በመውደቁ ምክንያት ሊታመን እንደማይችል ሰው አድርጎ ወደጎን አልጣለውም:: ዳግመኛም ይኸው ጴጥሮስ በአንጾኪያ ጳውሎስ ፊት ለፊት የተቃወመውን ተቃውሞ በመርሳት ስለእርሱ /ስለጳውሎስ/ ሲጽፍ /የተወደደው ወንድማችን/ ይላል /2ጴጥ.4:15/:: ይህም በጌታ አርአያ የተቀረጸ የእውነተኛ አገልጋይ ክርስቲያናዊ ሁኔታ ነው::

በመቀጠልም ጳውሎስ ትልቅ አብነት ነው፤ ስለሌሎች ሰዎች በደግነትና በፍቅር የተናገራቸውን ሁሉንም ነገሮችና አብረውት ስለሚሠሩት አገልጋዮች የሰጠውን ምስክርነት በጊዜ ውስጥ ማስታወስ ሊ ያቅት ይችላል፤ ሆኖም አንድ ሰው በሮሜ16፤ በ1ቆሮ.16፤ በቄላ.4 ስለተዘረዘሩት ሰዎች ማሰብ ይችላል:: ነገር ግን ጥቂት ምሳሌዎችን ለመምረጥ ያህል እንደሚከተለው እናያለን፤ እርሱ /ጳውሎስ/ ወጣት ወንድሞች በሆኑት በቲቶና በጢሞቴዎስ ላይ ያለውን መተማመንና ለእነርሱ በግል የተናገረውን ነገር እንዲሁም ለፊልሞና የጻፈውን የትህትና መልእክት አስቡ:: እነዚህ ሁሉ በክርስቶስ የሆነ አባትንና የበሰለ እውነተኛ ክርስቲያንን ያሳያሉ:: «ስለቲቶ የሚጠይቅ ቢኖር ስለእናንተ አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው፤ ስለወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተክርስቲያናት መልእክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው::» በማለት ይመሰክራል /2ቆሮ.8:23/:: ጢሞቴዎስንም በተመለከተ «ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ» በማለት ይጽፋል /1ቆሮ.4:17/:: ዳግመኛም በመልእክቲቱ መጨረሻ «ጢሞቴዎስም የመጣ እንደሆነ በእናንተ ዘንድ ያለ ፍርሃት እንዲኖር ተጠንቀቁ፤ እንደ እኔ ደግሞ የጌታን ሥራ ይሠራልና፤ እንግዲህ ማንም አይናቀው:: ነገር ግን ከወንድሞቹ ጋር እጠብቀዋለሁና ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ በሰላም በጉዞው እርዱት፤ ስለወንድማችን ስለ አጵሎስ ግን ከወንድሞቹ ጋር ወደ እናንተ እንዲ ሄድ እጅግ አድርጌ ለምኜው ነበር፤ ዛሬም ለመምጣት ከቶ ፈቃድ አልነበረውም፤ ሲመቸው ግን ይመጣል» በማለት ይጽፋል:: /1ቆሮ.16:10-12/ ስለአጵሎስ ሲናገር «አጵሎስ የተግባር ሰው አይደለም፤ ሁል ጊዜ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ የሚያይ ነው፤ እርሱን በመለመኔ አዝናለሁ» የሚል ቃል አልጨመረም:: አጵሎስ የጌታ አገልጋይ ነው:: የሚያገለግለውም በጳውሎስ ሥር ሆኖ ሳይሆን በጌታ ሥር ሆኖ ነው፤ ጳውሎስም ይህንን አውቆ እንዲሄድ ወይም እንዲቆይ የመወሰኑን ነጻነት ለእርሱው ይተውለታል:: በአጵሎስ በኩል ፈቃድ ቢኖር ያ የእርሱ ጉዳይ ነበር፤ በጳውሎስ በኩል ግን ትእዛዝም ሆነ የመቆጣት ዝንባሌ አልነበረም::

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በስድስት መልእክታቱ ውስጥ ከራሱ ጋር አብሮ እየጠቀሰ በመጻፍ በእርሱ እንዲህ ያለ መተማመን ነበረው /2ቆሮ.1:1፤

*(ወደ ገጽ 7 ይዞራል)*

## የፈርዖን ... *ከገጽ 2 የዞረ*

ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል» /2ተሰ2፡11-12/ ተብሎ እንደተጻፈው ሰዎች በጠማማ ሐሳብ ለመሄድ ሲወስኑ እግዚአብሔር እንደልባቸው ናፍቆት እንዲሆኑ ይተዋቸዋል። እውነት የሆነ ነገር እንዲቀበሉ ቀርቦላቸው እምቢ ሲሉ ያለጥርጥር ውሸትን በአማራጭነት ይቀበላሉ። ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኞች ካልሆኑ ሰይጣንን ይቀበላሉ። ገነትን እምቢ ካሉ ደግሞ የፈለጉት ሲኦልን ነው። የማያምን አእምሮ ይህ ስህተት ነው ሊል ይችል ይሆንን? ይህን ከማድረጉ በፊትም እንዲህ ያሉትና ይህ ፍርድ የተሰጣቸው ሰዎች ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን ያረጋግጥ፣ ለምሳሌ ያህል ፈርዖን በተገለጠለት ብርሃን መጠን ኃላፊነቱን መወጣቱን ያረጋግጥ፣ እንደዚሁ ማናቸውንም ሁኔታ ማረጋገጥ አለብን፣ ያለጥርጥር ይህን ማረጋገጥ ያለባቸው እግዚ አብሔር እውነትን በሚቃወሙት ላይ በሚወስደው የእርምጃ ዓይነት ላይ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ናቸው። ቀና ልብ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ግን በሰው ተመርምሮ በማይደረስበት የእግዚአብሔር መግቦት ውስጥ «እግዚአብሔር ጻድቅ ነው» ይላል፣ ከማያምኑ ሰዎች ለሚወረወሩበት ጥያቄዎችም አጥጋቢ መልስ መስጠት ባይችል እንኳን «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን አይፈርድምን?» /ዘፍ18፡25/ በማለት አእምሮውን ያሳርፋል። ሰውን ለማሳመን ከቀረበ ከሰው ሙግት ይልቅ በዚህ ዓይነት ችግርን በእግዚአብሔር ላይ በመጣል ያለው ጥበብ ይበልጣል። ምክንያቱም በተቃውሞ ለእግዚአብሔር መልስ የመመለስ ዝንባሌ ያለው ልብ ከሰው በሚቀርብለት የማሳመኛ ሐሳብ ሊያምን እንደማይችል እርግጥ ነውና።

እግዚአብሔር እንደ ኃያልነቱና እንደ ልዑልነቱ መጠን ለእያንዳንዱ የሰው ልጆች የትዕቢት ንግግር መልስ ሊሰጥ፣ ከፍ ያለውንም ሐሳባቸውን ከምድር ላይ ሊጥለው ሥልጣን አለው። «ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ተመድቦባቸዋል»/ዕብ9፡27/። ይህንን ፍርድ ማስወገድ አይቻልምና ከሞት የሚያመልጥ የለም። ነገር ግን ሰው ሽንፈቱን በተለያዩ መንገዶች ለመደበቅ ይሞክር ይሆናል። በሞት ሸለቆ የሮጠውን ሽሽቱን በተቻለው መጠን ጀግንነት ሊያስመስልና የኑሮውን የመጨረሻ የውርደት ደረጃ ራሱ በፈጠራቸው እጅግ የከበሩ ስያሜዎች ሊጠራው ይሞክራል። የሞትን አልጋ በውሸት ብርሃን ሊያሽበርቀው ይፈልጋል፣ መቃብሩን በልዩ ልዩ ነገሮች ለማስጌጥና የቀብር ሥነ ሥርዓቱን ደግሞ በደማቅ ሰልፍ ለማስዋብ ይጥራል። አሳፋሪ ታሪኩ ሊጻፍበት የተገባውን ውብ ሐውልት ከአፈሩ በላይ ያቆማል፣ ይሁን እንጂ ይህንንና ሌላውንም ሁሉ ቢያደርግ ሞት እንደሆነ ሞት ነው፣ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ከራሱ ሊያስወግደው አይችልም፣ ሞት «የኃጢአት ደሞዝ» የመሆኑንም እውነታ ሊያስቀር አይችልም። ፈርኦን የልቡ ጠንካራነት ምንም አልጠቀመውም ፍፃሜውን በከፋ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ሆነበት እንጂ።

እኛም ይህን ሳነበቡ ሁሉ የወንጌል ጥሪ ሲቀርብላቸው ልባቸውን እያደነደኑ እንሳስን።

## ጉበኞች፣ ...

*(ከገጽ 3 የዞረ)*

በጥንት ዘመን በታሪክ የምናውቀውን የትሮይን ከተማን ብናስብ የመጥፋቷና የውድቀቷ ምክንያት የጉበኞች ቸልተኝነት ነው። ሆሜር እንደጻፈው በግሪክና በትሮይ/ጢሮአዳ/ መካከል ለብዙ ጊዜ ጦርነት ተካሂዶ ነበር። ጦርነቱ በትሮይ ሜዳ ከከተማ ውጪ ሲደረግ ቢቆይም ግሪኮች የትሮይን ከተማ መስበር ለረጅም ጊዜ ተስኖአቸው ነበር። በመጨረሻም ትልቅ የእንጨት ፈረስ ሰርተው በትሮይ ሜዳ ላይ ትተው ወደ ግሪክ የተመለሱ መስለው በመርከብ ሄዱ፣ ሆኖም በእንጨት በተሠራው ፈረስ የተመረጡትን ጀግኖቻቸውን አድርገው ነበር ከከተማው ፈቀቅ ያሉት፣ የትሮይ ጠባቂዎች ግን ግዙፉን የእንጨት ፈረስ ውስጡን ሳይመረምሩ ወደ ከተማቸው አስገቡት፣ የሄዱ የመሰሉት የግሪክ ወታደሮች ሲመሽ ተመልሰው ከተማውን ተጠግተው ቆዩ። በእንጨት ፈረሱ ውስጥ የነበሩት የተመረጡት የግሪክ ወታደሮች ወጥተው የትሮይን ጠባቂዎች ገድለው የከተማውን በር ለወታደሮቻቸው ከፍተው ትሮይን አቃጠሏት፣ ሕዝቡንም አጠፉ ያች ትልቅ ከተማ ወደመች።» ከዚህ ከሆሜር ታሪክ እንደተረዳነው በጦርነት ያልተሸነፈች አገር በጉበኞች ጥንቃቄ ማጣት ጠፋች። በተቃራኒው በጉበኞች ሥራ በርካታ ሃገራት ከትልቅ ጥፋትና እልቂት ድነዋል። ዛሬስ ቢሆን የአንድ ሃገር ሕልውና በደህንነት ሠራተኞች ላይ የወደቀ አይደለምን? አሁን ያለችው እስራኤል ለመሰብሰብና አደጋ በበዛበት በዐረቡ አገራት መካከል ሆና ለብልጽግናዋና ለሰላሟ ምክንያት የጉበኞቿ ውጤት እንደሆነ በብዙ ጸሐፊዎች ይታመናል።

## ነቢያት እንደ ጉበኛ

ይህ የጉበኛው ተግባር በመንፈሳዊው አለም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአትና በሰይጣን እንዳይማረኩ እንዳይጠፉ እግዚ አብሔር ነቢያቱን ጉበኞች አድርጎ ይልክላቸው እንደነበር ከቃሉ ተመልክተናል። በይበልጥ በሕዝቅኤል ትንቢት በሁለቱም በም.3፡16ና 33፡3 ስፍራ ተብራርቶአል።

ሕዝቅኤል ይህንን ማስጠንቀቂያ በሚናገርበት በም.3፡16-33፡3 ጊዜ መካከል ኢየሩሳሌም በጠላት /በባቢሎን/ የተከበበችበት ጊዜ ነው፣ በባቢሎን የተደረገው የይሁዳ ምርኮ ሦስት ጊዜ ነው። 1ኛ.በ605 ከክ.በፊት፣ 2ኛ.በ597 ከክ.በፊት፣ 3ኛ.በ586 ከክ.በፊት፣ ሲሆን ሕዝቅኤል በሁለተኛው ምርኮ በዮአኪን ጊዜ ነበር የተማረከው፣ በምርኮ አብረውት ለነበሩት ኢየሩሳሌም እንደምትጠፋ መቅደሱንም እንደሚያፈርሱት ነገር ግን ነጻ የሚወጡበት ጊዜም እንዳለ ያጽናናቸው ነበር። በሕዝ.3፡16 «የሰው ልጅ ሆይ ለእስራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ» ብሎታል። በም.33 የመጨረሻው ምርኮ በተደረገበትም ወቅት እንደዚህ ባለ ማስጠንቀቂያ እግዚአብሔር በጉበኛ /በሕዝቅኤል/ በኩል ሕዝቡን ሲያነቃ እናያለን። ነገር ግን ሕዝቡ ከእውነተኞች ነቢያት ይልቅ ሀሰተኞቹን በማድመጥ በኃጢአታቸው መጥፋትን መርጠው ነበር፣ ለጉበኛው ጩኸት ግምት አልሰጡትም።

እግዚአብሔርም ለሕዝቅኤል ስለ ሀገር ጠባቂ/ጉበኛ/ ከነገረው በኋላ «አንተም፣ የሰው ልጅ ሆይ፣ ለእስራኤል ቤት ጉበኛ አድርጌሃለሁ፣ ከአፌ ቃሌን ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው» ብሎታል /ሕዝ.33፡7/ ሕዝቅኤል ሕዝቡን በኃጢአታቸው እንዳይጠፉ ከእግዚ አብሔር ቃል ያስጠነቅቃቸው ነበር፣ ጉበኛ መለከት እንደሚነፋ ህዝቅኤልም በእግዚአብሔር ቃል ነበር የሚያስጠነቅቃቸው። ጠላቶችም ሥጋውያን ጠላቶች አልነበሩም፣ ኃጢአትና የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊትም ጭምር ነበር እንጂ፣ ለውድቀትና ለጥፋት የሚዳርጉአቸው እነዚሁ ነበሩ። ስለዚህ ነቢያትን እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ጉበኛ አድርጎ አስነስቷቸው ነበር /ኤር.6፡13፣ ሆሴ.8፣ ዕን.2፡1/። ይሁን እንጂ እስራኤል በጉበኞቹ አልተጠቀመችም፣

*ወደ ገጽ 8 ይዞራል*

# ስለክርስቶስ አገልጋዮች …

(ከገጽ 5 የዞረ )

ፊልጵ.1፡1፣ ቈላስ.1፡1፣ 1ተሰ.1፡1፣ 2ተሰ.1፡1፣ ፊልሞ.1፡1/። ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲጽፍ «ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ እንዲለኝ ፈጥኜ ጢሞቴዎስን ልልክላችሁ በጌታ በኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደ እርሱ ያለ ስለኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ ማንም የለኝምና፤ ሁሉም የራሳቸውን ይፈልጋሉና፤ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም። ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንደአገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ» ብሏል/ፊልጵ.2፡19-22/። ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲጽፍ ደግሞ «ስለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋር አብሮ ለክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው» ብሏል/1ተሰ.3፡2/። ለራሱም ሲጽፍለት «በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ፣ … ለተወደደው ልጄ ለጢሞቴዎስ» ይላል /1ጢሞ.1፡2፤ 2ጢሞ.1፡2/። ስለጌታ አገልጋዮች የምናስበውን፣ የምንናገረውንና የምንጽፈውን በተመለከተ መንፈስቅዱስ አብነት በሆኑ ሰዎች በኩል ያስተማረን የጸጋና የፍቅር መንገድ ይህ ነው። እነርሱ ለእርሱ የተወደዱ ናቸው፣ ስለ እነርሱም መልካም ሲነገር መስማትም የተለየ ደስታን ይሰጠዋል። አንዲት የቤት ሠራተኛ ሰዎች ለእርስዋ መጥፎ ጠባይ ቢያላብሷት ልትጐዳ እንደምትችል ሁሉ እውነተኛ የክርስቶስ አገልጋይም የስም ማጥፋትና የሐሰት ወሬ ሲደርስበት ታማኝነቱ፣ መልካም ጠባዩና አገልግሎቱ ሊጎዳ ወይም ሊጠፋ ይችላል። ይህ እንዴት የሚያሳዝን ነው! ይህ እንዴት ኢክርስቲያናዊ ነው! የመተማመን ውሃ ያለበት ጕድጓድ ከተመረዘ የሥነ ምግባር ሞት የማይቀር ይሆናል።

ቤተክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ በተመለከተ ልንጠብቅ የምንችለው ማናቸውም መመለስ /ፈውስ/ መጀመር ያለበት እዚህ ስፍራና በዚሁ ነገር መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። «በመካከላችሁ የሚደክሙትን … ታውቁ ዘንድ ስለሥራቸውም ከመጠን ይልቅ ታከብሯቸው ዘንድ …» ይላል /1ተሰ.5፡12-13/። በጌታ ሥራ የሚደክም እያንዳንዱ አገልጋይ አብሮት ስለሚደክመው አገልጋይ በቸርነትና በፍቅር ያስብ፤ እርሱን እያደነቀው መልካም የሆነ ነገርን ይናገር፣ ይጻፍ። በዚህም የእርስ በእርስ አንድነት ከምንጩ እያደገ ይመጣል፤ ይህም የአንድነት ምንጭ የቃሉ አገልግሎት ነው። ስህተቶችን በማወጅ፣ ታላላቅ ክሶችን በማንሳት፣ መሠረት የሌላቸውንና መርዛማ ወሬዎችን በመቀበልና በማሰራጨት ፈንታ እያንዳንዱ ሰው ብዙ ኃጢአቶችን የሚሸፍን የፍቅር መሸፈኛ ሊይዝ ይገባዋል፤ የጌታን አገልጋዮች በተመለከተ ክፉ ወሬን መቀበል የለበትም፤ በተቃራኒው ግን የሐሰት ወሬ የያዙትንና ክፉ የሚናገሩትን በመቃወም መግታት እና የከበረው የክርስቲያን ፍቅር እንዲኖር መሥራት፣ ለወንድሞቹም መልካም ስም ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። በዚህም በቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ላይ የሚታይ የጸጋ መታደስ፣ የሥነምግባርም መመለስ በቶሎ ይመጣል።

በስኮትላንድ ውስጥ በጌታ ሥራ ላይ ስለነበረ ስለአንድ የተባረከ አገልጋይ እናት የተባለ ነገር አለ፤ ማንኛውም ሰው ስለአንድ ጎረቤት ወይም ወዳጅ ክፉ ወሬን ይዞ ከመጣ «ባርኔጣዬን አወርድና ስለእርሱ ይህንን ነገር ወደነገርከኝ ሰው እንሂድ፤ ስለጉዳዩም እናያለን፤ እውነት እንደሆነም እናጣራለን» ብላ ትናገር ነበር። በዚህ የታመነ አካሄድዋም ክፉ ተናጋሪዎችን ሁሉ ፍርሃት ውስጥ ያስገባች ሲሆን ከዚያ በኋላም በስም ማጥፋት ወሬዎቻቸው አልተቸገረችም። የልጅዋም ሕይወት በእናቱ የእውነተኝነት ክብር የተቃኘ ነበር፤ በእግዚአብሔር ጸጋ የክርስትናን እውነት ባወቀ ጊዜም ታላቅ የሆነ የቤተክርስቲያን ክንዋኔዎችን የፈጸመ ብቻ ሳይሆን ብዛት ያላቸውን ነፍሳት ወደ መዳን ያደረሰ የታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ዋነኛ ሰው ሆነ። ልክ እውነትን እንደምትወደው እንደዚህች እናትና እውነትን እንደሚናገረው ልጅዋ፣ በውስጣችን ያለ እውነት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ማድረግ የሚችል ይሁን፤ ይህም የሥነምግባር ለውጥን ያመጣል። በማገልገል የሚደክሙቱ ከእርስ በእርስ መካሰስ፣ የዚህን ወይም የዚያን ሁኔታ አስመልክቶ ራስን በማጽደቅ ከማልቀስም ነጻ ሆነው ሀሳባቸው፣ ጊዜያቸው፣ ቋንቋቸው ሁሉ በክርስቶስና በመልካም ነገር ሙሉ በሙሉ እንዲያዝ የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። የሚከስሰው የተከሰሰውን በማግኘት ፈውስን /መፍትሔን/ የማምጣት ሥራ ቢሠራ የጌታን ሥራ በሚሠሩ መካከል ያሉ ሁሉም ክፉ ተናጋሪዎች ሊጠፉ ይችላሉ። ይህ ግን ነገሩ በአደባባይ እንዳይገለጥ ከመፍራት ችግሩ ውጫዊ በሆነ መልኩ ብቻ እንዲያቆም ያደርግ ይሆናል። መሠረታዊው ፈውስ ውስጣዊ መሆን አለበት፤ በመንፈስም ሊሆን ይገባል። ተግባራዊ የሆነ ጽድቅ፣ ለወንድሞች ያለን ተግባራዊ ፍቅር፣ እና እነዚህን ነገሮች የሚያስገኘው ፍቅር ከእግዚአብሔር የመወለዳችን ማረጋገጫዎች ናቸው። /1ዮሐ.3/

በዚህ ርእስ ላይ ቃልን የመጻፍ አስፈላጊነትን ማሰብ አሳዛኝ ነው፤ ነገር ግን በዚህ መልካም ባልሆነና አጥፊ በሆነ ጠባይ ሁላችንም ይነስም ይብዛ በደለኞች አይደለንምን? እናቴ በጌታ ቀን ከሰአት በኋላ በቤተሰብ ክልል ውስጥ ድምፅዋን አሰምታ በምታነብ ጊዜ ስሰማው የነበረውን ርእሱ "Dyer's Golden Chain" «የወርቃማ ሰንሰለት ቀለም» የተባለ አንድ አሮጌ የቀድሞ ፕሮቴስታንት መጽሐፍን አስታውሳለሁ፤ ያኔ ምንም እንኳ ልጅ ብሆንም /እርስዋ በሞተች ጊዜ 13 ዓመቴ ነበር/፣ እናም በውስጡ ያለውን ትምህርት መውሰድ ባልችልም በውስጡ በሕይወቴ ሁሉ የነካኝና ወሳኝ ምልክትን የሰጠኝ አንድ ነጠላ አገላለጽ ነበር። ይኸውም ጸሐፊው ስለ ቤተክርስቲያን መልአክ ሲናገር በመጽሐፉ ውስጥ «አገልጋዮች መላእክት ተብለው የተጠሩት ባላቸው ክብር ምክንያት ነው፣ ነገር ግን መላእክት በወደቁ ጊዜ አጋንንት ሆኑ» ያለው ቃል ነው/1ዮሐ.3፡8-10/። «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በእርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፤… ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ። ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ። መራርነትና ንዴት ቍጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፤ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ» /ኤፌ.4፡25-32/።

## እነዚህን አስቡ

## በቀረውስ ወንድሞች ሆይ

- እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ
- ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ
- ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ
- ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ
- መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ
- በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን

**እነዚህን አስቡ**

**(ፊልጵ.4፡8)**

## ጉበኛው ... ከገጽ 6 የዞረ

እንዲያውም እንደ ኤርምያስ ያሉትን በብዙ መከራ አሠቃዩአቸው፤ በተቃራኒው የተሳሳተ መረጃ የሚሰጧቸውን ሐሰተኛ ጉበኞችን፣ ለጠላት የሚሠሩትን አደመጡ መጨረሻቸውም ወድቀት ሆነ::

ለእግዚብሔር ህዝብ ሰላምና ደህንነት ጉበኞች ትልቅ ቦታ እንደነበራቸውና ነቢያትንም ህዝቡን ከርኩሰት ለመጠበቅ ጉበኞች አድርጎአቸው እንደነበር ሁሉ እንዲሁም ጌታችን ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን ጉበኞችን ሰጥቷዋል::

«የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን? አለው:: አዎን ጌታ ሆይ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው:: ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው» /በዮሐ.21፡16/::

በመጀመሪያ ጴጥሮስ ይህንን አደራ ተቀብሎ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ከመሄዱ በፊት የቀረው ወሳኙ አደራ የበጐቹ ጉዳይ ነበር፤ ጌታ ኢየሱስ በደሙ የዋጃቸውን ነፍሳት እንደ ዐይን ብሌን ይመለከታቸዋል:: እነዚህ በዓለም ያሉ የእርሱ ወገኖች በማቴ.13፡44 የተጠቀሰው ያለውን ሁሉ ሸጦ የገዛው መዝገብ ናቸው:: ዓለምን በደሙ ቢገዛም በዚህ አለም የእርሱ ወድ ንብረት መሆን የቻሉት ቅዱሳኖቹ ናቸው:: ሳውልን «ስለምን ታሳድደኛለህ?»፣ «ቤተክርስቲያኔን»፣ «በጐቼን» ... ወዘተ» በሚሉ ቃላት የእርሱነታችንን የሚገልጠው ጌታ ለነፍሳት ያለው ግምት ከምናስበው እጅግ ላቅ ያለ እንደሆነ በቃሉ የምናነበው ሐቅ ነው:: ታዲያ የእነዚህን የበጎቹ ጉዳይ ከዕርገቱ በፊት ለስምኦን አደራ ሲሰጠው በጥብቅ አደራ 3 ጊዜ "ትወደኛለህን?" የሚል ጥያቄን በመጠየቅ ነበር:: አደራው ለጌታ /ለበጎቹ ባለቤት/ በሚኖር ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነበር:: ጌታ ስምኦን «በጎቼን ጠብቅ፣ አሰማራ» ያለው ለእርሱ ያለውን ፍቅር 3 ጊዜ ካረጋገጠ በኋላ ነበር::

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን አካባቢ ያለውን አገልግሎት ጨርሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ሳለ በዚያ መከራ፣ እስራት እንደሚቆየው በመንፈስ በተረዳ ጊዜ ሽማግሌዎችን ሰብስቦ ብዙ ከመከራቸው በኋላ፣ «በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።»/የሐዋ.ሥ20፡28/ በማለት ነበር ያስጠነቀቃቸው::

አሁንም ቤተክርስቲያን ከክፉ እንድትጠበቅ እንዲሁም ነፍሳት ከአለማዊነትና ከአጋንንት ትምህርት ይድኑ ዘንድ ይህ የጉበኞች ሸክም ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ለእረኞች የተሰጠ አደራ ነው::

በዘመናችን ያሉ ሐሰተኛ ጉበኞች /እረኞች/ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለጠላት ሲያጋልጡት ስንመለከት እውነተኛ ጉበኛው ወዴት ነው? ያሰኛል:: ጌታ ዛሬም እጅግ ብዙ ክርስቲያኖችን ሲመለከት እንደ ያኔው የአይሁድ ሕዝብ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጥለው ተጨንቀው ነው የሚመለከታቸው:: «ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለው ነበርና አዘነላቸው» ይላል /ማቴ.9፡36/ እኛም በዘመናችን የተጨነቁና የተጣሉ በጎችን ስንመለከት «ጉበኛው ሆይ ወዴት ነህ?» እንላለን::

በዚህ በእኛ ዘመን ከቃሉ የወጡ በርካታ እንግዳ የሆኑ ትምህርቶችና ልምምዶችን እናስተውላለን:: ብዙ አማኞች በጠላት ወጊያና ማታለል እየተወሰዱ እንዳሉ መረዳት ለሁላችንም ቀላል ነው:: ቀደም ባሉት ጊዜያት አማኞች ሲጸየፏቸው የነበሩ በዓለማዊነት የተበከሉ ልምምዶች ዛሬ እየተለመዱ መጥተው ምንም እንዳልሆኑ ሲቆጠሩ እናያለን፤ እንዲያውም በእንዲህ ዓይነት ዓለምን በወንጌል ስም ለውሰው የሚያቀርቡት እንደባለራዕይ ሲቆጠሩ ማየት የዕለት ከዕለት ትንግርት ሆኗል፤ በዓለም ካለው ቋንቋና ልማድ በመውሰድ «የመዝሙር ኮንሰርት፣ የአምልኮ ምሽት... » ተብለው ሥጋ ከዓለም ያጣውን በጭፈራ የሚገኝ ጊዜያዊ እርካታ በተዘዋዋሪ እንዲያገኝ የሚያደርጉ ዝግጅቶች በቸልታ ሲታዩ ወይም ሲፈቀድላቸው ማየት ጉበኞቹ ሕዝቡን ከሰይጣን ማታለል የማስጠንቀቅ ሥራቸውን ምን ያህል እንደተዉት የሚገልጽ ነው:: እንዲህ ያሉ ብዙ አሳፋሪ ልምምዶች ድነናል በሚሉት አገልጋዮች ዘንድ እየተሰበከ፣ እየተጠደረገና እየተስፋፉ መሆኑን ስንመለከት የእውነተኛ አማኝ ልብ በኀዘን መዋጡ እንደማይቀር እንረዳለን:: በዚያው በሐዋርያት ዘመን እንኳ «የቆሮንቶስን ቤተክርስቲያን በስነምግባር፣ የገላቲያ ክርስቲያኖች በተበላሸ ትምህርት፣ የዕብራውያን አማኞች ወደ ኋላ በመመለስ ወዘተ» ጠላት እንዴት ይዋጋ እንደ ነበር ማየት እንችላለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስለ ወደፊቱ በሚጽፍበት ጊዜ በአማኞች መካከል ክፉዎች ሰዎች በክፋታቸው እየባሱና እያሳቱ እንደሚቀጥሉ ነው ያሳሰበው /2ጢሞ.3፡14/:: በማቴ.13፡25 ጌታ በምሳሌ እንደተናገረው ጠላት በተዘራው መልካም ዘር መካከል እንክርዳድ የዘራው አገልጋዮቹ ሲተኙ አይደሉምን? ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ የነበረችው ቤተክርስቲያን ውድቀት እንዲሁ ነበር:: ከዚያ ሁሉ መከራ በኋላ አደራውን የተረከቡት እረኞችም በምቾት አልጋ ላይ መተኛታቸው ነበር ለከፋ ስህተት ቅዱሳኑን የዳረጉት:: አሁን ያለንበትም ከፍ ያለው ወይም ጣሪያ የደረሰው ብልሽት አብዛኞቹ የተገለጡት ያኔ ነበር:: ከዚያም በቤተክርስቲያን ዘመን ሁሉ የደረሱት አደጋዎች ዋነኛ ምክንያት የጉበኞች /እረኞች/ ቸልተኝነት ነበር::

ዛሬ ከመቼውም በበለጠ የጌታ መምጣት የቀረበበት ጊዜ ነው፤ ታዲያ ከእርሱ ዘንድ ዋጋችንን የምንቀበልበት፣ ከእርሱም ጋር ለዘላለም የምናርፍበት፣ ከእርሱም ጋር የምንነግሥበት ... ወዘተ ጊዜ ቀርቦአል:: ስለዚህ በዘመናችን የሚታየው ቅጥ ያጣ የአምልኮ፣ የዝማሬ፣ የአገልግሎት፣ ጠላት በጌታ ስም አማኞችን በሐሳቡ የሚያጠምድበትና የሚያታልልበት ሆኖ ሳለ፣ የዘመናችን ጉበኞች በዝምታ ማየታቸው በጌታ ዘንድ የሚያስጠይቃቸው ይሆናል፤ ጌታ ዛሬም ስለሚሰናከሉት ሰዎች «ደሙን ከእጁ እፈልጋለሁ ይላል»፤ ሆኖም ይህ ሁሉ ሲሆን እያዩ ልባቸው በኀዘን የተሰበረና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ የገባቸው በርካታ የጌታ ቅሬታዎች እንዳሉ ይታወቃል:: አንዳንዶቹም በተገኘው መንገድ ጬኸታቸውን እንደ እውነተኛ ጉበኛ እያሰሙ እንዳለ በተለያዩ መልኮች እያየን ነው፤ ታዲያ ከእኛም ጌታ የሚፈልገው ቢሰሙንም ባይሰሙንም እንደታማኙ ጉበኛ ሳንፈራ ስህተቱን ስህተት ነው በማለት አማኞችን ከጥፋት ልናስጠነቅቃቸው ይገባል፤ በመዝሙረኛው «ጽድቅን ወደድህ ዓመፅን ጠላህ» የተባለውን የጌታን ባህርይ እኛም የእርሱ የሆንን ልንለብሰው ይገባናል:: ጌታ ኢየሱስ ለጴጥሮስ «ትወደኛለህን?» ብሎ የጠየቀው ጥያቄ የክርስቶስን መንጋ በሚጠብቁት ጎሊና ውስጥ ሁል ጊዜም ሊታወስ ይገባል::

እውነተኛ የጌታ ልጆች የሆኑ ሁሉ በዓመፅ አይደሰቱምና በመጀመሪያ ራሳችን በአካባቢያችን በመንፈሳዊ ስም የተቋቋሙን መድረኮች በቃሉ እንመርምራቸው፤ ከዚያም ስህተት የሆነውን ስህተት በማለት አንዳንዶችን ነጥቀን ከእሳት እናድን /ይሁ.23/:: ምክንያቱም ዛሬ የምናየው አፍኣዊ ክርስትና እስራኤል በሕዝቅኤል ዘመን በነበረችበት የከፋ ደረጀ የደረሰ ይመስላል፤ ታዲያ እግዚአብሔር የዚህ ዘመን እረኞችን እንደ ሕዝቅኤል ቃሌን ትናገሩ ዘንድ ጉበኞች አድርጌአችኋለሁ ይላቸዋል:: ስለሆነም ከጌታ ጋር መነቀፍን መርጠን የተሰጠንን አደራ ልንወጣ ይገባል::

# የጌዴዎን እምነት

መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ የእምነት አባቶችን ገድልና አገልግሎት ያቀርብልሃል፤ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በዕብ.11፡32 እና በመሳ.6 በዝርዝር ከተገለጡት ሰዎች መካከል የጌዴዎንን አገልግሎት በተመለከተ እናጠናለን።

ጌዴዎን ለአገልግሎት /ሕዝቡን/ ለማዳን ሲጠራ በእምነት እግዚአብሔር በሚፈልገው መጠን ያደገ አልነበረም፤ ይልቁንም እጅግ ፈሪና ታናሽነቱን የተቀበለ ሰው ነበር፤ ግን ትልቁ እግዚአብሔር በጌዴዎን ትንሽነት ተጠቀመ። እግዚአብሔር በእርግጥ መከበር የሚፈልገው አንረባም፣ ትንሽ ነን፣ ባሉ ሰዎች ተጠቀሞ በሚሰራው ታላቅ ሥራ ነው፤ ወቅቱ እስራኤል ከምድያም እጅ በታች ሆነው ለሰባት ዓመት የተገዙበት ወቅት ነበር፤ ስለዚህም እስራኤል በምድያም ፊት የሚሠራው ሥራ አልነበረም፤ እህል የሚወቁት በወይን መጥመቂያ ተሸሽገው ነበር፤ በሌሊት እንጂ በቀን በድብቅ እንጂ በግልጽ ለመሥራት የማይችሉበት ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር ጌዴዎንን እስራኤልን ለማዳን የጠራው። ጌዴዎን እግዚአብሔር እየተናገረው እንኳ ዙሪያውንና የራሱን፣ የመታሰቡን ማንነት ነበር የሚመለከተው። በጌዴዎን ውስጥ ለእግዚአብሔር ሥራና ለራሱ ለእግዚአብሔር የማይመች ነገሮች ነበሩ፤ እግዚአብሔር ግን ባለጠጋ ስለሆነ ሊሠራ ሲፈልግ በመታገሥ ለክብሩ ተጠቀመበት፤ በጌዴዎን ውስጥ የነበሩት የግል ማንነቶችና ለእግዚአብሔር ፈጽሞ የማይመቹ ነገሮች እስኪጨረሱ ድረስ በጌዴዎን መጠቀም አይቻልም። በእርሱ ለመጠቀም የራሱን ባዶነት ማወቅ ነበረበት፤ ከመሳሪያነት በስተቀር በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ምንም ላደርግ አልችልም፣ እግዚአብሔርን ለማገዝ የሚያስችል ነገር የለኝም ማለት ነበረበት።

በመሳ.6፡11 ላይ «የእግዚአብሔር መልአክ በኦፍራ ባለችው ለአቢዔዝራዊው ለኢዮአስ በነበረችው በአድባሩ ዛፍ በታች ተቀመጠ፤ ልጁም ጌዴዎን ከምድያማውያን ለመሸሸግ በወይን መጥመቂያው ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር። እግዚአብሔር በራሱ ጉልበት ስለሚሠራ በፈሪ ሰው ይጠቀማል፤ ፈሪውን በራሱ ክንድ ደግፎና አቁሞ መክበር የሚፈልግ አምላክ ነው። በመሳ.6፡17-21 ጌዴዎን ከእግዚአብሔር ጋር በሚነጋገር ጊዜ ጥያቄዎችን ሲጠይቅ እንደነበረ እናነባለን። በመሳ.6፡22-24 ደግሞ «.. .. ወዮልኝ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና አለ። .. .. ጌድዎንም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ ስሙንም እግዚአብሔር ሰላም ብሎ ጠራው።» አዎ ሰውየው ወዮልኝ ብሎ የእግዚአብሔርን ትልቅነት ሲያውጅና የራሱን ትንሽነት ሲመለከት እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ በሰውየው መሥራት ይጀምራል። የራሱን ባዶነት ማየት እስኪጀምር ድረስ ይጠብቃል። በኢሳ.6፡5 ላይ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሲመለከት የራሱን ማንነት ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሲል፣ የሕዝቡን ማንነት አየና ራሱንና የሕዝቡን ድርጊት ሲኮንን እንመለከታለን። ሰው የእግዚ አብሔርን ከፍታ ከላየ የራሱን ትንሽነት ማየት ቢችልም በጥቂቱ ነው። እግዚአብሔር ሰው እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ይፈልጋል። ኢሳይያስ «ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለአዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ አልሁ» ማለት ከቻለ በኋላ እግዚአብሔር ለሥራው ኃይል ሲሰጠው፣ ከነበረበት ርኩሰት ሲያነጻውና ለአገልግሎት ሲልከው እናያለን። ጌዴዎንን ከመጥፋት የዳነው በመሠዊያ እንደሆነ ሁሉ ኢሳይያስም ከመጥፋት የዳነው ከመሠውያው በጉጠት የተወሰደው ፍም ነበር፤ ጌዴዎን የራሱን ማንነትና ድካም ከጨረሰ በኋላ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ ደረጃ ደረሰ፤ መሥዋዕቱን የበላው የእግዚብሔር በትር፣ ጌዴዎን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን እንዳገኘ የምናውቅበት መሳሪያ ነው። እግዚአብሔርም ጌዴዎን የራሱን ትንሽነት ካወቀ በኋላ በእርሱ መሥራት ቀጠለ፤ እኔ ምንም አይደለሁም ካለ በኋላ ሥራውን ጀመረ፤ ትንሹ የጌዴዎን ማንነት ጨርሶ እስክትጠፋ ድረስ እግዚአብሔር ጌድዎንን አስጨረሰው። የእግዚአብሔር ሥራ በእኛ ውስጥ ባለ ትልቅም ሆነ ትንሽ አቅም አይለካም። ያላረፈች ነፍስ ማረፍ እስክትችል እግዚአብሔርን ማገልገል አይቻላትም። ያላረፈች ነፍስ በእግዚአብሔር ትምህርት ቤት በሕይወታችን የምንማርበት ሁኔታ ውስጥ ገብታ ካልወጣች የእግዚአብሔርን አንዳች ሥራ መሥራት አትችልም።

ጌዴዎን «ወዮልኝ» ካለ በኋላ የራሱ ማንነትና አቅሙ ሁሉ ከጠፋ በኋላ እግዚአብሔር ሥራ ጀመረ፤ ፈሪ የነበረው ጌድዎን ወደ አስገራሚ ለውጥ ሲመጣ እናያለን።

«እግዚአብሔር ሰላም» ካለ በኋላ ወደ ተጠራበት አገልግሎት ሊሄድ ይዘጋጃል። በዚህ ጊዜ ብዙ ችግር ባለበት ሁኔታ እግዚአብሔር ሰላም ነው ማለት ከቻለ ይህ ችሎታ ከእግዚ አብሔር ያገኘው ነው።

በመሳ.2.25-32 የጌድዎንን ስም መለወጥና ትርጓሜውን እናገኛለን። ይሩበአል ማለት በአል ከእርሱ ጋር ይምዋገት ማለት ነው፤ ጌዴዎን በጠላት ላይ ያደረሰው ጥፋት ብዙ ነው፤ ይህ ሥራው ደግሞ ከአባቱ ጀምሮ ሁሉም ሰዎች በእርሱ ላይ እንዲነሡ የሚያደርግ ነበር፤ ጌዴዎን አባቱ ፈርቶ ነበር፤ ምክንያቱም የአባቱ የሆነውን የበዓል መሠዊያ ነውና ያፈረሰው። ጌዲዎን አሁን ሥራውን ከቤቱ ጀምሮአል፤ የአባቱ የሆነውን መሠዊያ አፍርሷል፤ የጠላትን ሥራና ጉልበት በሰው ፊት ማቅለል፣ ክፋትና አማፃን ምንም ጉልበት እንደሌለው ከቤት ጀምሮ እስከ አደባባይ ማጋለጥ ያስፈልጋል። ጳውሎስ «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ» ጳውሎስ /2ቆሮ.12፡1፤ 12፡10/።

ወገኖቼ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በሰው መሥራት ይፈልጋል፤ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ በራሱ ኃይል ብቻ ነው፤ ስለዚህ በቅድሚያ እኔ ምንም አልችልም/አልጠቅምም/ እስክንል ድረስ ያስተምረናል። «ወዮልኝ ጠፍቻለሁ» የሚለው ደረጃ ላይ ሰው ሲደርስ እግዚአብሔር ሥራውን ይጀምራል። ለጌዴዎን የተሰጠው ተልዕኮ እጅግ ከባድና ዋና /የመጀመሪያ/ የሆነውን የበአል መሠዊያ ማፍረስ ነው። ስለፈራ በሌሊት ተነሳና መሠውያውን አፈራረሰው። የሚፈራው አባቱንና ቤተሰቡን፣ የከተማውን ሰው ሁሉ ነው። እየፈራም ቢሆን፣ በሌሊት የሰይጣን ዙፋን ያለበትን መሠዊያ አፈራረሰው።

እግዚአብሔር ሰላም የሚለው መሠውያ የእግዚአብሔር መሠዊያ ሲሆን ጌዴዎን ያን በመጀመሪያ አቁሟል፤ የበአልን መሠዊያ ግን በማፍረስ የአደባባይ ምስክርነት ሰጠ።

ጌዴዎን ምንም እንኳ ፈርቶ የሠራው ቢሆንም የበአልን መሠዊያ ማፍረስ በራስ ላይ መጨከንን ያሳያል። ይህንን ሥራ ማንም አልደፈረውም። እርሱ ግን የከባዱ ሥራ ጀማሪ ሆኖ ተነሳ። ብዙ ጊዜ ሰዎች መነሻ /ጀማሪ/ ለመሆን አይፈልጉም። በሌሎች ላይ

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

# ጊዜና ዘላለም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ውስጥ የተቀመጡት የእውነት መርሆዎች እጅግ የከበሩና ሕይወትን የሚመረምር ጠባይ ያላቸው ናቸው:: ለእነዚህ መርሆዎች ተግባራዊ ምላሽን መስጠት በአሁኑ ጊዜ እጅግ የበዛ ጥቅም አለው:: በዚህ በተገለጸው እውነተኛ በሆነው ብርሃን ውስጥ ዓለማዊ ፍትወትና ሥጋዊነት ሊኖሩ አይችሉም፤ ከሥራቸውም ይደርቃሉ:: አንድ ሰው ለዚህ እጅግ ውድ ለሆነው የመነሻ ሃሳብ ክፍል አጠር፣ ጠቅለል ያለና ግልጽ ርዕስ እንዲሰጥ ቢጠየቅ «ጊዜ! ከዘለዓለማዊነት አንጻር» ብሎ ሊጠራው ወይም ርዕስ ሊሰጠው ይችል ይሆናል:: ነገሮች ሁሉ በዚህ ዓለም ከሚገኙበትና ከሚታዩበት በፍጹም ተቃራኒ በሚሆኑበት በዚያኛው ዓለም ብርሃን ውስጥ ደቀመዛሙርቱን ሊያኖር ጌታ በግልጽ ሲያቅድና በማይታዩት ነገሮች ቅዱስ ተጽእኖ ሥር ልባቸው እንዲሆን ሕይወታቸው በሰማያዊ መርሆዎች ኃይልና ሥልጣን ይያዝ ዘንድ ነው::

## ከግብዝነት ተጠበቁ /ቁ.1/

እንደዚህ ዓይነቱ የታመነ መለኮታዊ መምህር ሐሳብ እጅግ ከፍ ላለው ትምህርቱ «አስቀድማችሁ ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ፣ እርሱም ግብዝነት ነው» በማለት እጅግ ተፈላጊነት ባላቸው ቃላት ጠንካራ መሠረትን አስቀምጧል:: በነፋስ ውስጥ ማዕበል ወይንም የሚያናጋ ነገር መኖር የለበትም፤ ጥልቅ የሆኑት የሰው ልጅ የሐሳብ ምንጮች ሁሉ ወደ መገለጥ መምጣት ይኖርባቸዋል:: ንጹሕ የሆነውን ሰማያዊ ብርሃን ወደ ሥነምግባራችን ጥልቀት ውስጥ ዘልቆ ይገባ ዘንድ ልንፈቅድለት ይገባናል:: ስውር በሆነው የነፍስ ፍርድና በቋንቋ አመራረጣችንና አጠቃቀማችን መካከል ማለትም ከመንገዱ በተዛባው ሕይወታችንና በከንፈራችን ምስክርነት መካከል ልዩነት እንዲኖር አይጠበቅም:: በአጭሩና ጠቅለል ባለ አገላለጥ በተለይም ከዚህ ተግባራዊ እውነትነት ካለው ትምህርት ተጠቃሚና ትርፋማ እንሆን ዘንድ ከታማኙና መልካሙ ልብ የመነጨው ጸጋ ያስፈልገናል::

ይህን እውነት በቀዘቀዘ ስሜት ወይንም በቸልታ እንድንሰማ የተገባ አይደለም:: ልንወደው አንችል ይሆናል:: ቀለል ያለ የቅዱሳን መጻሕፍትን ሐሳቦች፣ ትምህርቶችንና ትንቢቶችን የመምረጥ ዝንባሌ በብዙዎች ዘንድ ይስተዋላል:: ምክንያቱም እነዚህን ከተለያዩ የዚህ ዓለም ሐሳቦች ከምኞት ልምምዶች /ከመጐምዠት ልምምዶች/ እና የራስን ጥቅም ከመፈለግ ጋር በቀጥታ በማያያዝ ስለሚጠቅሙ ሊሆን ይችላል:: እውነት በእውነትነቱ በቀላሉ መቀበል ሊያዳግት ቢችልም፣ ይህ የእውነት መርህ ግን በማንኛውም ሐሳብ ላይ በፍጥነት የመገለጥና ሥጋዊ ነገሮችን የመቁረጥ ኃይልና ሥልጣን ያለው በጸጋው ራሳቸውን ከፈሪሳውያን እርሾና ግብዝነት ሊያነጹ የሚፈልጉትን ሁሉ የሚደግፍና የሚያድን ነው:: ይህ እርሾ እጅጉን የማስመሰል ፀባይ ያለውና በተለያየ ቅርጽ ወይንም ዓይነት ስለሚገለጥ በጣም አደገኛ ነው:: በእርግጥ በሚገኝበት ስፍራ በነፍስ ተሞክሯዊ እውቀትና ልምምዳዊ ቅድስና እድገት ፊት ሊወጡት የማይቻል መሰናክል ይኖራል:: ሙሉ በሙሉ ማንነታችንን ለመለኮታዊ እውነት ሥራ አሳልፈን ካልሰጠን ከዚህ ከመለኮታዊ ብርሃን እራሳችንን ወደ ሌላኛው ጥግ ወይንም ወደራሳችን ጉድጓድ በመግባት የምንሸሽ ከሆነ የተደበቁና እግዚአ ብሔር የማይከብርባቸውን የራሳችንን፣ ነገሮች ብቻ የምንከባከብ ከሆነ ተአማኒነት በጐደለው ሁኔታ እውነትን ለራሳችን የግል ልምምዶች ማጠናከሪያ ለማዋል የምንፈልግ ከሆነ፣ ሐሳባችንን የእርሱ ባልጩት እንዳያርፍበትና እንዳያስተካክለው የምንሸሽና የምንከላከል ከሆነ በእርግጥም በግብዝነት እርሾ እንደተነካካንና እንደተበከልን ብሎም በመንፈሳዊ እድገታችን በፍጹም ክርስቶስን መምሰል እንደማንችል ያሳያል:: ስለዚህም የክርስቶስ ደቀመዝሙር ለሆነ ሁሉ ከዚህ ክፉ እርሾ አንዳችም ነገር ወደ ልቡ የምስጢር ክፍሎች ይገባ ዘንድ እንዳይፈቅድ ይጠበቅበታል:: እርሾው ከእኛ ይርቅ ዘንድ እኛም በሁሉም ሁኔታ «ጌታ ሆይ፣ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር» ማለት እንችል ዘንድ የጌታ ጸጋ ይርዳን::

ግብዝነት መንፈሳዊ ሕይወትን ማበላሸት ብቻ ሳይሆን የመንፈሳዊ ህይወትን ዓላማ የሚያስጥልም ነው:: «የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለምና» እንደተባለው የእያንዳንዱ ሰው ሃሳብ ወደዚህ ብርሃን ይመጣል፣ እያንዳንዱንም ሰው ይህ በተገለጠው እውነተኛ ብርሃን ስፍራውን እንዲያውቅ ያስችለዋል:: ይህም አሁን እውነት የሚያደርገው ነገር ሲሆን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ግን በመጨረሻ ላይ በሚገባ ይገለጣል፤ ግብዝነትም ሆነ ማንኛውም ውጤት ከክርስቶስ የፍርድ ወንበር በሚወጣ ብርሃን ይገለጣል::

አንዳችም ነገር ከዚህ ብርሃን እንዲያመልጥ አይፈቀድለትም:: ምንም እንኳን አሁን ያለውና እየሆነ ያለው ከዚህ በተለየ በተቀራኒው ቢሆንም በኋላ ግን እውነትነቱ የተረጋገጠ ይሆናል:: በተጨማሪም እያንዳንዱ ነገር የራሱ በሆነ ስም ባይገለጥም የራሱ ያልሆነውንና ያልተገባውን ስፍራ ቢይዝም በዚያን ጊዜ ግን ሁሉም በትክክል የራሱንና ሊይዝ የተገባውን ስምና ስፍራ ይይዛል:: በዚህ ዓለም ሐሳብ መያዝ ጠንቃቃነት ሁሉንም የመያዝና የምኞት መንፈስ መያዝ የአርቆ አስተዋይነት ችሎታ የሚፈልጉትን በማድረግና ራስን ማርካት እንዲሁም ያለአግባባ በሆነ ራስን ማበልጸግ እንደፍትሐዊ አስተዳደርና በሥራ ውስጥ የሚታይ የተመሰገነ ትጋት ተደርጐ የሚቆጠርበትን ሁኔታ እናያለን:: እነዚህ ነገሮችም ይህንን የተሳሳተ ሥፍራቸውንና ስማቸውን እንደያዙ የሚቀጥሉት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው፤ ነገር ግን ወደፊት ሁሉም ከዚህ ፍጹም ተቃራኒ በሆነ በትክክለኛ ማንነትና ምንነታቸው ይገለጣሉ:: በክርስቶስ ወንበር ፊት ሁሉም ነገሮች በትክክለኛው ቀለማቸውና መልካቸው ሲታዩ በተገቢው ስማቸውም ይጠራል:: ስለዚህም የልብ ሁሉ ምስጢር በሚገለጥበት በዚያን ጊዜው ብርሃን አንጻር ነገሮችን ሁሉ ማየት፣ እንደሚገባ መመላለስና የሚገባውን ሁሉ መፈጸም የማንኛውም እውነተኛ ደቀመዝሙር ጥበብ ሊሆን ይገባዋል::

ስለዚህም ከፍ ባለ መሠረት ላይ የቆመው ሐዋርያው «መልካምም ቢሆን ወይንም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል::» አለ /2ቆሮ.5፡10/:: ይህ አገላለጥ የደቀመዝሙርን አእምሮ ይረብሽ ይሆን? ልቡን ከግብዝነት እርሾ ሁሉ

ወደ ገጽ 11 ይዞራል

## ጊዜና ዘላለም ...*(ከገጽ 10 የዞረ)*

ካጸዳ ታላቅ መሠረትነት ባለው ሥፍራ፣ በተጠቀሰው የእግዚአብሔር ትምህርት/አስተምህሮ/ በሆነው እውነት ላይ እንደሚገባ ነፍሱን ወይም ማንነቱን ካኖረ በእርግጠኝነትም ሊረበሽ ወይም ሊፈራ አይችልም። ክርስቶስ ሕይወቱ እንዲሁም ጽድቁ ነውና። ስለዚህም ህይወቱ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ያን ጊዜ እርሱም ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ይገለጣል። ስለዚህም ጳውሎስ «ለእግዚአብሔር ግን የተገለጥን ነን፣ በህሊናችሁም ደግሞ የተገለጥን እንደሆንን ተስፋ አደርጋለሁ ይላል»። /ቈላ.3፡4፤ 2ቆሮ.5፡11/»

## እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አትፍሩ /ቊ.4-5/

ነገር ግን ጳውሎስ ራሱ በህሊና ሰላምና በልብ ታማኝነት የመገለጥ ችግር ቢኖርበት በፍርድ ወንበር ፊት መገለጥ የሚለው ሐሳብ መንፈሱን እጅግ ሊያውከው እንደሚችል ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ስለዚህም ጌታ በሉቃስ ምዕራፍ 12 ውስጥ «ለእናንተም ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፣ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ የሚበልጥ ሊደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ። እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፣ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ፤ አዎን እላችኋለሁ እርሱን ፍሩ።» በማለት የደቀመዛሙርቱን ህሊና /ሐሳብ ሁሉ/ በቀጥታ ወደ ፍርድ ወንበሩ ብርሃን ሲያመጣውና በዚያም ለዘወትር ይሆን ዘንድ እንደሚፈልግ እናነባለን። «ሰውን መፍራት ወጥመድ ነው»። ይህም ከፈሪሳውያን እርሾ ጋር በእጅጉ ይያዛል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው። ይህም ሰው ሁልጊዜ ከፍርድ ወንበሩ ብርሃን አንጻር እንደሚገባ እንዲያስብ፣ እንዲናገር፣ እንደሚገባም እንዲመላለስ ያደርገዋል። በራሱ መደገፍንና የኩራት መንፈስ፣ ነፍስን ሁሉ እያንዳንዱን ነገርም ሆነ ማንነት እንዲገለጥ በሚያደርገው መለኮታዊው ብርሃን ሥር ማድረግ /ማኖር/ ከጅማሬው ሕመም ቢኖረውም ታላቅ ክብርና ከፍታን የሚያመጣ ነው።

የክርስቶስ ደቀመዝሙር የሆነ በሰዎችና በዚች ዓለም ክፋት ፊት በመመላለሱና በመገኘቱ ትክክለኛውን የደቀመዝሙርነት ስፍራውን ሊቀማው የሚችል አንዳችም ነገር አይኖርም። እኛ በሰማይ ያለው ጌታችን ተከታዮች በዚች ዓለም እስካለን ድረስ ለማንኛውም የዚህ ዓለም ነገር የተፈታንና መብት ያለን አይደለንም። በሰዎች ፊት የሚኖረው ክፉ ምልልስ ከሥነምግባር አንጻርም ቢሆን መንገዳችንን ከእግዚአብሔር ለማራቅ ከሚፈልገው ክፋት ጋር ተባባሪ ነው። ሁለቱም ክፋቶች ከፈሪሳውያን እርሾ ተካፋይ የሆኑና ሁለቱም በፍርድ ወንበሩ ፊት ትክክለኛ/ተገቢ/ ስፍራቸውን ያገኛሉ። ስለምን ሰዎችን እንፈራለን? የእነርሱ ሐሳብስ ስለምን እኛን ይመለከተናል? ወደ ገሃነም የመጣል ሥልጣን ባለው በክርስቶስ ክብር /መገኘት/ ፊት ሐሳባቸው በፍጹም መቆም የማይችል ከሆነ እነርሱ ምንም ሥፍራ ሊሰጣቸው የሚገባ አይደሉም፤ ስለዚህ እኛ መኖርና መሥራት የሚገባን ከእርሱ ጋርና ለእርሱ ብቻ መሆን አለበት።

ሰው በአሁኑ ጊዜ በሌሎች ላይ የሚፈርድበት የራሱ የፍርድ ወንበር ሊኖረው ይችላል፤ ወደፊት ግን ይህ የፍርድ ወንበር ሊኖረው አይችልም። ሰው ጊዜያዊ የራሱን ፍርድ ቤት ሊመሠርትና ሊፈርድ ቢችልም ዘለዓለማዊ የሆነ የፍርድ ቤት ሊኖረው ግን አይችልም። ታዲያ ራሳችንን ለምንድነው እጅግ ደካማና ፈጥኖ በሚጠፋ በዚህ ዓለም ፍርድ ብቻ የሕይወታችን መለኪያ በማድረግ ለዚህች ዓለም በሚስማማ ሁኔታ የምንመላለሰው? ከዚች ዓለም ክፉ ነገሮች ለመለየትና ወደፊት ከሚሆነው ከርሱ ፍርድ አንጻር በአዎንታዊ መልኩ የሚስማማ ሥራን መሥራት እንድንችል ልባችንን ሙሉ በሙሉ ሊለወጥ ይገባዋል። ሁሉንም ነገራችንን ከዘለዓለማዊው ብርሃን አንጻር ማየት እንድንችልም ጌታ ጸጋውን ያብዛልን።

የሰዎች ሐሳብና አመለካከቶች እኛን የማይመለከቱን ከሆነ የዚህ ዓለም ሃሳብና አመለካከቶች /ፍልስፍናዎች/ እጅግ በበዙበት ዓለም ውስጥ መኖር የምንችለውና እንደሚገባ መመላለስ የሚቻለው እንዴት ነው? በማለት ምስኪንና ሙሉ በሙሉ ያልታመነ ልብ ሊጠይቅ ይችላል። ይህም በጣም የተለመደ ጥያቄ ነው፤ ነገር ግን ሙሉና የሚያረካ መልስን ከከበረው መምህራችን ከንፈሮች ይገኛሉ። ጌታ ደቀመዛሙርቱን ከማያምን ማንነት ከሚመነጩ የዚህ ዓለም ነገሮች እና እንደሚገባ እንዳይመላለሱ ከሚያውክ በመንፈሳዊ ህይወታቸውም ላይ መደብዘዝን ሊያመጣ ከሚችል ጭንቀት እንዳይጨነቁና በእርሱ ላይ መደገፍ እንደሚገባቸው ሲነግራቸው እንዲሁም ግልጽ ወደሆነና ድንግዝግዝን ማስወገድ ወደሚችለው ብርሃን ሲያመጣቸው እንመለከታለን። ጌታም «አምስት ድንቢጦች በአስር ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም። ነገር ግን እናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳን የተቆጠረ ነው፣ እንግዲያስ አትፍሩ፣ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ /ቁ.6-7/። ልባችን ከዚህ የመጽሐፉ ክፍል መማር ያለበት እግዚአብሔርን እንድንፈራ ብቻ ሳይሆን በእርሱ እንደምንጠበቅና ደግሞም እንደሚንከባከበን እንድናውቅ ጭምር ነው፤ ማስጠንቀቅ ብቻም ሳይሆን ሲያረጋጋቸው እናነባለን።

«ፍሩ» እና «አትፍሩ» የሚሉት ሁለቱ ቃላቶች ለሥጋና ደም እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ቃላት ቢመስሉም ለእምነት ግን የሚስማሙና የሚደጋገፉ ናቸው። አብዝቶ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ሌሎች ነገሮችን የሚፈራው እጅግ ትንሽ በሆነ መጠን ነው። የእምነት ሰው በዚች ዓለም ውስጥ እጅግ ጥገኛ ያልሆነ ሰው ነው። በእግዚአብሔር ላይ እጅጉን ጥገኛና በእርሱ የሚደገፍ ሲሆን በዚች ዓለም ነገሮችና ሁኔታዎች ላይ ፈጽሞ የማይደገፍ ነው። ሁለተኛውም የመጀመሪያው ውጤት ነው።

የአማኞች የሰላም መሠረትንም አስቀምጧል። ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለው ብቻውንም ሊፈራ የተገባው ጌታ የትኛውንም አማኝ ስለራሱ ጠጉር ጭምር እንኳን ሊጠነቀቅለት እርሱ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን ወስዷል። ጌታ ይህንን ኃላፊነት ሲወስድ አማኙን ዛሬም ቢሆን ወደፊት እንዲጠፋ ይተወው ዘንድ አይደለም። ትንሿ ወይም ጥቂቷ የአባታችን ጥበቃ በልባችን ውስጥ ሊነሣ የሚችለውን ማንኛውንም ጥርጥርና እያንዳንዱን ሁከት/ማዕከል/ ጸጥ የማድረግ ብቃት አላት። ለእርሱ ለጌታ በጣም ትንሽ ወይንም በጣም ትልቅ የሚባል ነገር የለም። ወይንም በሌላ አገላለጽ ለጌታ የሚከብድ ወይንም የሚቀል ነገር የለም። ቁጥር የሌላቸው ወሰን በሌለው ህዋ ውስጥ የሚሽከረከሩት እጅግ ግዙፍ የምንላቸው ፕላኔቶችም ሆኑ በሰማይ ላይ የሚበሩት ትንንሽ ድንቢጦች በእርሱ ዘንድ ልዩነት የላቸውም። እርሱ በማይወሰነው እውቀቱ በዘላለም ዘመን ውስጥ ያለምንም ድካምና መጓደል የራስ ጠጉራችንን ጭምር የመንከባከብ ብቃት አለው። ይህም «አትፍሩ» ደግሞም ስለአንድም ነገር «አትጨነቁ» የሚለው የክርስቶስ ቃል የማይነዋወጥ ወይንም የማይናጋ መሠረትነት ያለው ነው። በተከታታይ መለኮታዊ መርሆዎችን በሥራ ላይ የማዋልና በሕይወታችን የመተግበር ችግር ይታይብናል። መለኮታዊ መርህን እንደ መርህ ልናቅደው እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን ይበልጥ እውነተኛ የሆነ ውበቱን ልናይና ሊሰማን የሚችለው በሕይወታችን ስንገልጠው ብቻ ነው።

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

## ጊዜና ዘላለም ... *ከገጽ 11 የዞረ*

በተግባር ላይ የማናውለው ከሆነ በሸራ ድንኳን ላይ ሙቀት ሊሰጥ የማይችል የፀሐይ ጮራን/ጨረርን/ ስዕል ስሎ እጅግ በረሃብና በቅዝቃዜ ተቆራምዶ በውስጡ የተቀመጠ ሰውን እንመስላለን::

## ምን እንድትመልሱ አትጨነቁ /ቀ.11/

አሁን በዚህ በፊታችን ባቀረብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ከሰው ሐሳብ በላይ የሆነውን የተቀደሰውን ክብር ግልጽና በማንኛውም ሁኔታ ለድርድር ሊቀርብ በማይችል መልኩ ከክርስቶስ ምስክርነት ጋር ተያይዞ ቀርቦልናል:: እንደዚሁም በሕይወታችን ተዘልለን በሰላም እንድንኖር የሚያስችለንን የአባታችንን ደግነትና ጥበቃ እናነባለን:: ልባችንን ከዚህች ዓለም ከሆነው ፍርሃትና ከሰው ሃሳብ ተጽእኖ በላይ ካደረግንና የራሳችንን ጠጉር እንኳን ሳይቀር ግድ በሚለውና የእኛን ኃላፊነት በወሰደው በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ተረጋግተን የምንኖር ከሆነ በሰዎች ፊት ክርስቶስን ለመግለጥና ስለእርሱ ለመመስከር እንችላለን/ቁ.8-10/:: ስለሚኖረንም ምስክርነት እርሱ እራሱ ልናደርግና ልንናገር የሚገባን ነገር ሁሉ ይሰጠናል:: የምስክርነት ሥፍራችን የተጠበቀ እንዲሆን ይረዳናል:: «ወደ ምኩራባቸው ያመጧችኋል፤ ወደገዥዎችም ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ፣ አሳልፈውም ሲሰጧችሁ የምትናገሩት በዚያ ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንደምትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩት እናንተ አይደላችሁም» ተብሏል:: ብቸኛውና ትክክለኛ ለሆነው ለክርስቶስ የሚኖረን ምስክርነት መሠረቱ ከሰዎች ተጽእኖ ሥር ሙሉ በሙሉ መላቀቅና ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነው:: በሰው ሐሳብ ተጽእኖ ሥር ይበልጥ እየሆንን በመጣን መጠን ለክርስቶስ አገልጋይነት የሚኖረን ብቃት እየወረደ ይመጣል፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ከዚህ ተጽእኖ ሥር ማምለጥና ነጻ መሆን የምንችለው በእግዚአብሔር በሚኖረን ከፍ ያለ እምነት ነው:: ልባችን በእግዚአብሔር ነገር ሲያዝና ሲሞላ ለፍጥረታዊው የዚች ዓለም ሐሳብ ሥፍራ ሊኖረው አይችልም:: ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር የሚያስጨንቁንን ነገሮች ከእኛ ሊያስወግድ የቻለ ወይንም የሚችል ማንም እንደሌለ በፍጹም እርግጠኞች መሆን ይጠበቅብናል:: እግዚአብሔር ብቻውን ይህን ማድረግ ስለቻለና ደግሞም ወደፊት ስለሚችል ከማንም በላይ በእርሱ እንታመናለን:: ለማንኛውም አፋጣኝ ጉዳይ ትንሽም ይሁን ትልቅ እግዚአብሔር ብቻውን በቂ ነው:: እኛም እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን በማወቅ ብቻ በእርሱ እንደገፍ::

እግዚአብሔር ሰውን እንደ መገልገያ መጠቀሙ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰዎች ላይ፣ መሳሪያውን ከሚጠቀሙበት እጆች ይልቅ በመሳሪያው ላይ የምንደገፍ ከሆነ በራሳችን ላይ መርገምን እናመጣለን:: «በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልብንም ከእግዚአብሔር የሚመልስ ሰው ርጉም ነው»/ኤር.17:5/ ተብሎም ተጽፏልና::

ጌታ እግዚአብሔር ኤልያስን ይመግቡት ዘንድ ቁራዎችን ተጠቅሟል፤ ነገር ግን ኤልያስ በቁራዎቹ ላይ የመደገፍ ሐሳብም ሆነ ዝንባሌ አልታየበትም:: ይህ ነው በእኛ ህይወትም ለዘለዓለም ሊሆን የሚገባው:: እምነት በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ከእርሱ ብቻ መጠበቅ ወደ እርሱ መጠጋትና እርሱን መከተል በእርሱም ላይ እምነትን መጣል እርሱ እግዚአብሔር ብቻ እንደወደደ ይሠራ ዘንድ ሥፍራን መስጠት ማንኛውንም ፍጥረታዊ ድጋፍ በመፈለግ የጌታ የነጠረ መንገድ እንዳይነቀፍ ማድረግ ሙሉ በሙሉ የእርሱ የጌታ የከበረ እውነት በማንነቱ ይገለጥ ዘንድ መፍቀድና ሁሉንም ነገር ለእርሱ መተው አለበት:: እግዚአብሔር እጅግ የተወደደና በዚች ዓለም የእርሱንና የሰውን በአገባቡ እንድንለይ የሚያስችለንና ተገቢውንም ስፍራችንን የሚሰጥ ነው:: ይቀጥላል

---

## የጌዴዎን ... *ከገጽ 9 የዞረ*

አይተው አረጋግጠው ነው መግባት የሚፈልጉት:: በተለይ በእንደዚህ የጠላት ኢላማ በሆነ ጉዳይ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልጉ ብዙ አይገኙም:: ብዙ ጊዜ ባለቀ ሥራ ላይ መረባረብ /መነሳት/ ይቀላል:: በተለይ ተቃውሞ የሚያስነሳ የሚያስከስስ በሰው የሚያስንቅ ከሆነ ቀዳሚ ለመሆን የሚፈልግ ፈጽሞ ይታጣል፤ መከራና ተቃሙሞ የሚያስነሳ ከሆነማ ከኋላ ነው የምንጀምረው፤ ተደብቀንና ተመሳስለን ከቆየን በኋላ፣ የኋላ አርበኛ ለመሆን ቀና ደፋ እንላለን:: ጌዴዎን ትልቁን ጠላት ቀዳሚና ብቻውን ሆኖ ተጋፈጠ፤ እግዚአአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ስለነበር መከናወን ሆነለትና በኋላ ሕዝቡ ሁሉ ከእርሱ ጐን ቆመ::

ወገኖቼ አሁንም በክርስትናው ዓለም ብዙ የበኣል አምልኮዎች አሉ፤ ገንዘብ፣ የተከበሩ ሰዎች፣ ታሪክና ዘመን የሚጠቅስላችው ከስዕል ጀምሮ በርካታ አምልኮ ከባህል ከቤተሰብ የተወረሱና ጥንቃቄ የሚደረግላቸው የበኣል አምልኮዎች አሉ::

ጌድዎን ሥራ የጀመረው የአባቱን መሠውያ በማፍረስ ነው:: /መሳ.6:25/ ጌዴዎን አባቱን ቢሰብከው ኖሮ በሥራው ላይ ቀዳሚ መሰናከል ይሆንና ሊያስወግረው ይችል ነበር፤ ምክንያቱም በኣል በአባቱና በቤቱ እንዲሁም በአሕዛብ መካከል የሚፈራና የሚከበር ነበርና እንዴት ደፈርከኝ ልታስገድለኝ ነው በማለት አባቱ ይነሳበት ነበር፤ ቢያማክረውም ሊገድለው ይችል ነበር:: ነገር ግን ጌዴዎን ምንም እንኳን አንድም ሰው አጠገቡ ባይኖርም እግዚአብሔርን አምኖና ተመክቶ ቀዳሚ ሆኖ በመውጣት በኣል ምንም የማይችል ራሱን ሊከላከል የማይችል እንዲሁ ብቻ አስፈሪ ሆኖ ለዘመናት የተቀመጠ ግዑዝ አምላክ እንደሆነ በሥራው ገለጠው፤ ጌዴዎን በሌሊት ተደብቆ ነው በኣልን /የሰይጣንን ዙፋን/ ያፈረሰው:: እግዚአብሔር አንዳንዴ በድብቅ ሥራ ያስጀምራል፤ ለሌላው ሳይናገር ለባለ ሥራው ብቻ በመግለጥ ያስጀምራል፤ በዚህ አደገኛ ሥራ የተነሳ ሰይጣን የከተማውን ሰው ሁሉ በጌዴዎን ላይ ግልብጥ ብሎ እንዲነሳ አደረገ:: ራሱ ሰይጣን በከፍተኛ ቁጣና በቀል ከዙፋኑ ተነቃነቀ::

የተሠራው ሥራ በጌዴዎን እንደተሠራ ተመርምሮ ተደርሶበታል፤ ማስረጃ ተገኝቶበታል፤ ሁሉም መስክሮበታል:: አንድ ፈሪ በሠራው ሥራ ቁጥሩ እጅግ የበዛ የምሥራቅ አገር ሰዎች ሁሉ ተሰበሰቡ:: ምድያማውያን አማሌቃውያን ሁሉ ተከማቹ /መሳ.7:12/:: ብዛታቸው እንደ አንበጣ፣ የግመሎቻቸው ብዛት ቁጥር የሌለው እንደ ባህር አሸዋ፣ (በዚህ ሁሉ ግመል የተጫነውን ዕቃና ጦር መገመት ነው) ይህ ሁሉ በአንድ ሰው ላይ የተደረገ መሰባሰብ ነበር፤ አንድን ሰው ለማጥፋት ሰይጣን ያዘመተው ሠራዊት ነበር:: ጌታን ታምነን ሥራ ስንጀምር ከጠላት ሰፈር የሚረዳን ይነሳል:: አባቱ ለጌዴዎን ተሟገተ፤ እንዲሞት ልጅህን አውጣ ሲሉት በኣል ለራሱ ይምዋገት እርሱ አምላክ ከሆነ ለራሱ ይምዋገት አላቸው 6:31::

እግዚአብሔር የበኣልን ሠራዊት ካየ በኋላ እርሱን ባመነው ጌዴዎን ላይ መንፈሱን አወረደ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ገባበት:: ሰይጣን በጠላቱ ላይ ለዘብተኛ ሆኖ አያውቅም የእግዚአብሔር ቅናት ባለባቸውና በኃይል በሚነሡ ላይ በጣም ይቆጣል፤ በቁርጠኞች ላይ በፍጥነት ይነሳል:: ሰይጣን ለዘብተኛ የሚመስለው በቁርጠኝነት ባልተነሱና በመመሳሰል በሚኖሩ ሰዎች ነው፤ በእነዚህ ላይ ተመሳስሎ ቋንቋቸውን በመናገር ይገባና ለዘብተኛ ይመስልና ወደራሱ ለመመለስ ይተጋል:: ጌዴዎን

*ወደ ገጽ 13 ይዞራል*

## ጌዴዎን *... ከገጽ 12 የዞረ*

*ማንም ያላሰበውንና ሊሞክረው የማይችለውን ሥራ ሲጀምር ሰይጣን ብዙ ሰውን አሰነስቶበታል።*

*ጌዴዎን የእግዚአብሔር መንፈስ ከገባበት በኋላ ቀንደ መለከት ነፋ /መሳ.6:34/። ቀንደ መለከት አዋጅ ነው ... የክተት ጥሪ ነው። የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ እንዲነሳ ማወጅ ነው። እስከ አሁን ያየነው የጠላትን ኃይልና ብዛት፣ አሰላለፍ፣ የትጥቁን ሁኔታ፣ በቁርጥ የመውጣቱን ነገር ነበር። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል በጠላት ሥራ ላይ መንቀሳቀስ ጀመረ። ከእግዚአብሔር የሆኑት የአቢዔዝርም ሰዎች ተጠርተው ከእግዚአብሔር ሰው ኋላ ተከተሉ። ወደምናሴም ነገድ ሁሉ መልእክተኞችን ሰደደ፤ እነርሱም ተከተሉት። ወደ አሴር፣ ወደ ዛብሎን ወደ ንፍታሌምም ሰደደ፤ እነርሱም ሊገናኙአቸው ወጡ /መሳ.6:33-35/። እግዚአብሔር በኋላ ተነስቶ ሁሉንም ይቀድማል፤ ያሸንፋልም።*

*እግዚአብሔር ለአንድ አገልግሎት የጠራው አማኝም እንደጌዴዎን ለእግዚአብሔር ሰልፍ ራሱን ማዘጋጀት አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አገልግሎት መንፈሳዊ ሰልፍ እንደሆነ ተገልጧል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ውስጥ ይህን በተደጋጋሚ ጽፏል። ገና ከጅምሩ በ1ጢሞ.2:18 ውስጥ «ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ አስቀድሞ ለአንተ እንደተነገረው ትንቢት በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን አደራ እሰጥሃለሁ።» ይለዋል። እንዲሁም ብዙ የስህተት አሰራሮችና ክፉ ሠራተኞች ባሉበት ሁኔታ በሚሰጠው የወንጌል አገልግሎት እንዲጸና ሲመክረው «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል» በማለት ያበረታታዋል/1ጢሞ.6:12/። በወንጌል ምክንያት ሊደርስበት በሚችለው መከራ ውስጥ በጽናት እንዲያልፍ ሲመክረው ደግሞ «እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል» ይለዋል/2ጢሞ.2:3/ ስለዚህ የወንጌል አገልግሎት ከጠላት አሠራር ጋር የምናደርገው ሰልፍ ዋነኛ መገለጫ ነው። ነገር ግን ጌዴዎን በእምነት የጠላት ዋነኛ ምሽግ የሆነውን የበአልን መሠዊያ ካፈረሰ በኋላ ወገኖቹን መለከት በመንፋት ለሰልፍ ሲጠራ እንዳየነው ራሳችንን ለጌታ ሥራ በአግባቡ ካዘጋጀን በኋላ ሌሎች የታመኑ ሰዎችም አብረውን በወንጌል ሰልፍ ውስጥ እንዲጋደሉ ጥሪ ማስተላለፍ ይኖርብናል። ለዚህ የከበረ ጥሪ ምላሽ ከሚሰጡት ጋር በእምነት ብንሰለፍ ውጤቱ በምድያማውያን ላይ የተገኘው ዓይነት ድል ይሆናል።*

## አንዳንዶች የእግዚአብሔርን መኖር ለምን ይክዳሉ?

*አንድ የቅርብ ጊዜ የግጥም ፀሐፊ ከጥቂት መጣቶች ጋር በምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ ሳለ፣ ወጣቶቹ ስለ እግዚአብሔርና ስለሃይማኖታዊ ጉዳዮች እያነሱ ይነጋገሩ ነበር። ሁሉም በንግግራቸው ውስጥ በእግዚአብሔር መኖር /ህልውና/ የማያምኑ* (atheists) *መሆናቸውን ተናገሩ። ገጣሚው ለጥቂት ጊዜ በእርጋታ ሲያዳምጣቸው ከቆየ በኋላ «ወዳጆቼ በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ» በማለት ንግግሩን ጀመረ። የመጀመሪያዎቹ ነገሮችን በጥልቀት የሚመራመሩ፣ የጥንታዊውም ሆነ የዘመናዊው ፍልስፍና ማህበርተኞች የሆኑና በፍልስፍናቸው ከእውነተኛው መንገድ ወጥተው እግዚአብሔርን የካዱ ናቸው። ምናልባት እንደዚህ ዓይነቱ ጥልቅ ምርምርና ፍልስፍና ወደዚህ ጉዳይ አምጥቷችሁ እንደሆን አላውቅም አላቸው። እነሱም ነገሮችን በጥልቀት ከሚያጠኑት*(deep thinkers) *እንደማይመደቡ ከገለጡለት በኋላ ንግግሩን በመቀጠል ሁለተኛ ዓይነቶቹ ደግሞ ነገሮችን በሚገባ መለየት የማይችሉና ከሌሎች የሰሙትን ተቀብለው እየደጋገሙ የሚያስተጋቡ* (parrot-fashion) *ናቸው። እርግጠኛ ነኝ! ከእንደዚህ ዓይነቶቹም የምትመደቡ አይመስለኝም አላቸው። እነሱም ቁጣ ባዘለ ድምፅ እኛ ከእንደዚህ ዓይነቶቹም አይደለንም ብለው መለሱለት። እርሱም እንግዲህ መልካም የሦስተኛ ዓይነቶቹን ልንገራችሁ፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ደግሞ በጎ ሕሊናና አስተሳሰብ የሌላቸው በክፋት በተሞላ ሕይወት ውስጥ ያለፉ ከዚያም የቆሸሸ ሕይወት ላለመውጣት ጻድቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ህልውና ስለማይፈልጉ እግዚአብሔር የለም በማለት ለራሳቸው ምቾትን የፈጠሩ የሚመስላቸውና እንደልባቸው ሃሳብ በኃጢአት ውስጥ መዋኘታቸውን መቀጠል የሚፈልጉ ዓይነቶች ናቸው አላቸው። በመጨረሻም ወዳጆቼ አለ ገጣሚው «አራተኛ ዓይነት ግን የለም» ብሏቸው በዛለ መንፈስ ከተቀመጠበት ስፍራ ተነስቶ ትቷቸው ሄደ።*

## መዝሙሩ እና እረኛው

*ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ የጥበብ ማሳያ አዳራሽ ውስጥ ከእንግሊዝ ግንባር ቀደም ተዋናይ አንዱ ለተሰበሰበው ሕዝብ አንድ መዝናኛ እንዲያቀርብ ተጠየቀ። እርሱም ፈቃደኛ በመሆን ተመልካቹ ምን መስማት እንደሚፈልግ ጠየቀ። ከጥቂት ሰከንድ ፀጥታ በኋላ አንድ በዕድሜ ገፋ ያለ ቄስ ወደ እርሱ መጥቶ ጽጌረዳ አበባ ካበረከተለት በኋላ እንዲህ አለው። «እባክህ ጌታዬ ሃያ ሁለተኛውን መዝሙር ልትዘምርልን ትችላለህ?»*

*በተዋናዩ ፊት ላይ የመገረም ሁኔታ ታየ፤ ለሰከንድ ዝም ካለ በኋላ እንዲህ አለ፦ «እችላለሁ አንድ ነገር ግን እንስማማ እኔ ካቀረብኩኝ /ከዘመርኩኝ/ በኋላ አንተ ደግመህ ትዘምራለህ።» አለው። በሚያስገርም ሁኔታ ታላቁ ተዋናይ መዘመር ጀመረ የድምፅ አወጣጡና ቅላጼው የሚያስደንቅ ነበር። ተመልካቹ በተመስጦ ያዳምጠው ነበር፤ እናም ልክ ሲጨርስ ተመልካቹ በጭብጨባ አድናቆቱን ገለጸለት። ከዚያ ተዋናዩ ሲቀመጥ ቄሱ ተነሳና መዘመር ጀመረ። ድምፁ ያን ያህል የሚያስደምም አልነበረም፤ ቅላጼውም ቢሆን ችግር ነበረበት። መዝሙሩን ዘምሮ ሲጨርስ ምንም ዓይነት የአድናቆት ድምፅ አልተሰማም፤ ነገር ግን የሁሉም ሰው ዓይን በእንባ ተሞልቶ ነበር፤ ብዙዎቹም በታላቅ አድናቆት ተሞልተው ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ነበር።*

*ታላቁ ተዋናይ እንደገና ብድግ አለ። ራሱን መቆጣጠር እስኪያቅተው ድረስ እየተንዘፈዘፈ የቄሱን ትከሻ ያዘና ለተመልካቹ እንዲህ አለ፤ «ወዳጆቼ እኔ ጆሮአችሁንና ዓይናችሁን መሳብ ቻልኩኝ፤ ይህ ሰው ግን ልባችሁ ውስጥ ደርሷል። ልዩነቱም ይህ ነው፦ እኔ ሃያ ሁለተኛውን መዝሙር አውቃለሁ፤ ነገር ግን እሱ እረኛውን ያውቀዋል»*

# የጥያቄዎቻችሁ መልሶች

በጌታ ፍቅር የምንወዳችሁ አንባብያን በዚህ የጥያቄና መልስ ዝግጅት በመንፈሳዊ ሕይወት ለመታነጽና በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ለማደግ የሚያግዙ ትምህርቶችን እንደምታገኙ ተስፋ እናደርጋለን። በመሆኑም በዚህ እትም የብዙዎች ጥያቄ ይሆናሉ ብለን ባሰብናቸውና በመዳን ትምህርት ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሰጡት መጽሐፍቅዱሳዊ መልሶችን አቅርበንላችኋል፤ በማስተዋል እንድታነቧቸው እንጋብዛለን።

**ጥያቄ 1**

***መዳን የሚገኘው በእምነት ነው ወይስ መልካም ሥራን በመሥራት?***

***መልስ***

መዳን የሚገኘው በእምነት መሆኑን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይናገራሉ፤ ጥቂቶቹም እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

- «በልጁ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም» /ዮሐ.3፡36/።
- «ኢየሱስም መለሰ አላቸውም ... እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው»/ዮሐ.6፡47/።
- «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ» /የሐ.ሥ.16፡31/።
- «አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፤ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚ አብሔር ጽድቅ ነው»/ሮሜ3፡21-22/።
- «መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አይቶ በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ»/ገላ.3፡8/።
- «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታወቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ» /1ዮሐ.5፡13/።

መጽሐፍ ቅዱስ መዳን የሚገኘው በእምነት መሆኑን የሚገልጸውን ያህል በሥራ እንደማይገኝም በአጽንኦት ይናገራል፤ ይህንንም በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ እናያለን።

- «ሰው <u>ያለ ሕግ ሥራ</u> በእምነት እንዲጸድቅ እንቈጥራለንና»/ሮሜ3፡28/።
- «... ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ ሥጋን የለበሰ ሁሉ <u>በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ</u> እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል» /ገላ.2፡16/።
- ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሏልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው»/ገላ.3፡11/።
- «ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ <u>ከሥራ አይደለም</u>/ኤፌ.2፡8/።
- «... ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታ ጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ <u>እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም</u>»/ቲቶ3፡4-5/።

ስለዚህ ከእነዚህ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መዳን የሚገኘው በእምነት እንጂ በሥራ እንዳልሆነ በግልጽ እንግራለን። ይህም የሆነው ሥጋ የለበሰ ሁሉ ሕግን መጠበቅ ባለመቻሉ ምክንያት እግዚአብሔር መዳንን በጸጋው ስላደረገው ነው።

እንዲህ ሲባል ግን መዳናችን ለመዳን ብለን የምንሠራው መልካም ሥራ የለም ማለት ነው እንጂ ከዳንን በኋላ የምንሠ ራው መልካም ሥራ የለም ማለት አይደለም። አንድ ተክል ከጸደቀ በኋላ ፍሬ እንደሚያስገኝ የዳነ ወይም የጸደቀ ሰውም የመልካም ሥራ ፍሬዎች ይታዩበታል። ይህም በአምልኮ፣ በአገልግሎት እንዲሁም በሥነምግባር ፍሬዎች የሚገለጥ ይሆናል።

**ጥያቄ 2.**

***ታዲያ መዳን በሥራ ካልሆነ ለምንሠራው መልካም ሥራ ከጌታ የምናገኘው ምንድነው?***

***መልስ***

በእምነት መዳንን ካገኘን ወይም በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ከሆንን በኋላ የምንሠራው መልካም ሥራ ይኖራል። ይህንን በተመለከተም «እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» ተብሎ ተነግሮናል /ኤፌ.2፡10/። ለዚህም መልካም ሥራችን ወደፊት በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደየሥራችን በብድራት የሚከፈለን ዋጋ አለ። ይህም «መልካምም ቢሆን ክፉ እንዳደረገ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና» ተብሎ ተገልጿል /2ቆሮ.5፡10/። በሌላም ስፍራ «ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና» ይላል /ሮሜ14፡10/። በእነዚህ ንባቦች ውስጥ «ሁላችን» የሚለው ቃል ጸሐፊው ጳውሎስ ራሱን ጨምሮ መናገሩን ያሳያል፤ ጳውሎስ የዳነ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን የሚቀበሉ ሁሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ጳውሎስን ጨምሮ ሁላችን የምንቀርብበት ይህ የክርስቶስ የፍርድ ወንበር የመዳን ያለመዳን ጉዳይ ገና የሚረጋገጥበት ዙፋን ሳይሆን የዳኑ ሰዎች በሥጋ ዘመናቸው ለሠሩት ሥራ ተገቢው የጽድቅ ብድራት የሚከፈልበት የፍርድ ወንበር ነው። ስለዚህ በመልካም ሥራችን የምናገኘው መዳንን ሳይሆን እንደየሥራችን የሆነ ብድራት ወይም ዋጋ ነው። ይህም «የማይጠፋ አክሊል» መሆኑ የተገለጸ ሲሆን /1ቆሮ9፡15/፣ በ2ጢሞ.4፡8 ላይ «የጽድቅ አክሊል»፣ በያዕ.1፡12፤ ራእ2፡10 ላይ «የሕይወት አክሊል»፣ በ1ጴጥ.5፡4 ላይ «የክብር አክሊል» ተብሎ ተጠርቷል።

# በረከተ ጥበብ

## የሰው ጥያቄዎች?? እና የእግዚአብሔር መልሶች

♦ ***እኔ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ ነኝ?***
⇒ «እንግዲያስ እያንዳንዳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን፡፡» /ሮሜ.14፡12/

♦ ***እግዚአብሔር ሁሉ ነገሬን ይመለከታል?***
⇒ «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ አይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው፡፡» /ዕብ.4፡13/

♦ ***እርሱ እኔን በኃጢአት ተጠያቂ ያደርገኛል?***
⇒ «... መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል፡፡» ገላ.3፡22

⇒ «ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል፡፡» ሮሜ.3፡23

♦ ***ኃጢአተኛን ይቀጣል እርሱ?***
⇒ «ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፡፡»/ሕዝ.18፡4፤
⇒ «የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው፡፡» /ሮሜ.6፡23/

♦ ***እኔ እጠፋለሁ ማለት ነው?***
⇒ «.... ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወደ ስለእናንተ ይታገሳል፡፡» /2ኛ.ጴጥ.3፡9/

♦ ***እንዴት ከጥፋት ማምለጥ እችላለሁ?***
⇒ «..... በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ ፡፡» ሐዋ.16፡31.

♦ ***አሁን በዚህ ጊዜ መዳን እችላለሁ?***
⇒ «.... እነሆ የተወደደው ሰአት አሁን ነው እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው፡፡» /2ኛ.ቆሮ.6፡2/ አሁን

♦ ***ድኛለሁ? አልጠፋም ማለት ነው?***
⇒ «..... ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፡፡»/ዮሐ.6፡37/

## መታለሉ ይብቃ

ህይወት ትርጉም አልባ
ህይወት በባዶነት
ሲቃትት በድርቀት
ኑሮ ሆኖ ዝቅጠት
ጣም የለው እርካታ
መደዴና ተርታ፡፡
ፈርሶ ናዝራዊነት
ተስዕሎ ህዝብነት
ህይወት ሲሆን መና መላቅጥ ሲጠፋ
ሌላ ናዘራዊነት ሌላ አለም ፍለጋ፤
እንደነ ኑኃሚን
በሞዓብ ለማደር
እንደ ሎጥ በሰዶም ድንኳንን ማዛወር
በተለየ ራዕይ ከአለም ጋር መጣመር፡፡

የነፍስ ማቃሰት
በቃል ጥማት ድርቀት
መንፈሳዊ ራብን በምናብ ለማጥገብ
አእምሮን በማድከም ሥጋን በማዋከብ

በትርታ ልብን
በ'ሪትም' እጅ እግርን
በመዝሙር ዳንኪራ ለማግኘት እርካታ
ጉሮሮ እስኪነቃ በጩኸት በእሪታ
ለሥጋ ሆነለት ከዓለም ባጣው ፈንታ

በመንፈስ መቃጠል በመንፈስ መነዳት
በመንፈስ መዘምር በመንፈስ መደሰት
እግዚአብሔርን መምሰል
ላይመጣ በስሜት፣
ጭፈራና ጩኸት
ላያመጣ እድገት
እንዲሁ ባዶነት
ራስን የማሳት ምናባዊ ህይወት፡፡

ስለዚህ እንንቃ
መታለሉ ይብቃ
በመንፈስ እንሁን ከስሜት እንውጣ
በሕይወታችን ውስጥ
ለውጥን ቶሎ እናምጣ፡፡

# የእግዚአብሔር በግ

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካለው ፍቅር የተነሣ በኃጢአት ምክንያት ከእርሱ የተለየውንና የራቀውን ሰው ሊያድነውና ከእርሱ ጋር ኅብረት ሊያደርግ ሲፈልግ በሰው ፊንታ ቤዛ ሆኖ የሚሞት መሥዋዕትን አዘጋጀለት፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ስለኃጢአታቸው የበግ መሥዋዕትን በማቅረብ ወደ እግዚአብሔር ይቀርቡ ነበር፤ ይሁንና ያ የበግ መሥዋዕት /ዘሌ.4፡27-35/፡፡ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርባቸው መሥዋዕቱን ባቀረቡበት በዚያ ጊዜ ብቻ ሲሆን ስርየት የሚያገኙትም የአቅራቢው ኃጢአት ብቻ ነበር፤ በዓመት አንድ ጊዜ በሚከበረው በስርየት በዓል ስለእስራኤል ሕዝብ የሚቀርበው የኃጢአት መሥዋዕትም ቢሆን ስርየት የሚያስገኘው የእስራኤልን ማኅበር ኃጢአት ብቻ ነበር እንጂ የዓለምን ኃጢአት አልነበረም/ዘሌ.16/፤ እንደዚህም ሆኖ ለጊዜው ወደ እግዚአብሔር ለመቀረብ የሚያስችል ከመሆን አልፎ የብሉይ ኪዳን የእንስሳት መሥዋዕት ኃጢአትን ማስወገድ አልቻሉም ነበር፡፡ ይህን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር ‹የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና› ይላል/ዕብ.10፡4/፡፡

በዚህ በጸጋው ዘመን ግን እግዚአብሔር የአንድን አማኝ ወይም የእስራኤልን ኃጢአት ብቻ ሳይሆን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ መሥዋዕት ለሰው ልጅ ሰጥቷል፤ ይህንንም «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ኃጢአታቸውን ለተናዘዙ ሰዎች አስተዋውቋል፡፡ በዚያ ወቅት በቤተመቅደሱና በመሠዊያው ዙሪያ የነበሩት ፈሪሳውያንና ተከታዮቻቸው ሰውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ አገልግሎት መስጠት አልቻሉም ነበር፤ ጊዜው በአይሁድ ዘንድ የውድቀት ጊዜ ነበር፤ ከእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዝ ይልቅ የሽማግሌዎች ወግ የሚጠበቅበት፣ ግብዝነትና አስመሳይነት የበዛበት፣ በሌላው ኃጢአት ላይ የሚፈርዱ ሰዎች ራሳቸው ያንኑ ኃጢአት የሚያደርጉበት ዘመን ነበር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠውን ልጁን ለእስራኤል ለመግለጥ የመጥምቁ ዮሐንስን የምስክርነት አገልግሎት አዘጋጀ፡፡ ብዙ ሰዎችም ኃጢአታቸውን በመናዘዝ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤ ይሁንና በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ በሕጉ መጽሐፍ እንደታዘዘው ስለኃጢአታቸው በእነርሱ ፊንታ ኃጢአታቸውን ተሸክሞ የሚሞትላቸውን የበግ መሥዋዕት አላቀረቡም ነበር፤ ስለኃጢአታችን የቀረበ የበግ መሥዋዕት የት አለ? የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፤ መጥምቁ ዮሐንስ ግን ‹ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ› «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎ ልብን የሚያሳርፍ ምስክርነት ሰጣቸው፡፡ በዚህም «የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳንን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ» ብሎ አባቱ ዘካርያስ ስለእርሱ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ /ሉቃ.1፡77/፡፡

ዛሬም በየሥርዓት አምልኮው በሚከናወኑ የተለያዩ ሥርዓቶች እንዲሁም እጅግ በዝቶ በሚታየው መንፈሳዊ ውድቀት የተነሳ በኃጢአታቸው እየተጨነቁ ወደ እግዚአብሔር ለመቀረብ ያልቻሉ ብዙ ሰዎች በውድቀት ዘመን እግዚአብሔር ያዘጋጀው ይህ የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ለማስወገድ ለዓለም ሁሉ ከሰጠው ከራሱ በግ ጋር ማገናኘት ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር በግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለእርሱ አስቀድሞ «ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም» የሚል ቃል በትንቢት ተነግሯል /ኢሳ.53፡7/፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ ያነብ የነበረውም ስለእግዚአብሔር በግ የሚናገረው ይህ የመጽሐፍ ክፍል ነበረ፡፡ ወንጌላዊው ፊልጶስም ከዚህ መጽሐፍ ጀምሮ ስለኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት፤ እርሱም በኢየሱስ አምኖ በመጠመቅ በታላቅ ደስታ ወደ አገሩ ተመለሰ /የሐ.ሥ.8፡26-39/

በሮሜ 6፡23 ላይ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» ተብሎ ተጽፏል፤ በዚህ እውነታ ምክንያት ኃጢአተኛነታቸውን የሚያውቁ ሁሉ በሞት ፍርሃት ተውጠው ሲጨነቁ ይኖራሉ፤ ነገር ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ በመምጣት በቀራንዮ መስቀል ላይ ኃጢአታችንን ሁሉ በአንጨት ላይ ተሸክሞ ለሰው ሞቷል፤ ስለሆነም በኃጢአትና በሞት ፍርሃት ውስጥ ያሉ ሁሉ ኢየሱስ የሞተው ስለእኔ ነው ብለው ቢያምኑ እነርሱ እንደማይሞቱ ስለሚያውቁ ከዘላለም ሞት ይድናሉ፤ በምትኩ ግን የዘላለም ሕይወትን ይቀበላሉ፡፡ ቃሉ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» ካለ በኋላ «የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው» ይላል፡፡ ስለዚህ በቀደመው ኪዳን የነበረው ኃጢአተኛ እጁን በበጉ ላይ ጭኖ ራሱን ከመሥዋዕቱ ጋር እንደሚቆጥር ሁሉ/ዘሌ.4፡29፣33/ ዛሬም በወንጌል የተጠራ ማንኛውም ኃጢአተኛ በቀራንዮ ላይ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ከቀረበው የእግዚአብሔር በግ ጋር ሲቈጥር ወይም በእምነት ከክርስቶስ ጋር ሲሰቀል ይገባዋል፡፡ ያን ጊዜም የእግዚአብሔር ጽድቅ ለእርሱ ይቈጠርለታል፡፡ የዘላለም መዳንን ወይም የዘላለም ሕይወትን ያገኛል፡፡

## የሚከተሉትን መንፈሳዊ መጻሕፍት ያንብቡ

1. ደብተራ ኦሪት/የኦሪት ድንኳን/
2. ወደ ክርስቶስ ስም መሰብሰብ
3. የዕብራውያን መልእክት ትርጓሜ
4. ጦማረ ጽድቅ/የጽድቅ ደብዳቤ/
5. የኦሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ
6. መንፈስቅዱስ አካል ያለው መለኮት ነው
7. የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
8. የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜ
9. መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን
10. የመጽሐፈ ሩት ትርጓሜ
11. የእውነትን ቃል በአግባቡ መለየት
12. የወንጌል አገልግሎት
13. የአዲስ ኪዳን አምልኮ
14. የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን
15. ታቦት
16. በጌታ በኢየሱስ ስም የሚሰበሰቡክር ስቲያኖች
17. ታውቃለህን?
18. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና መንግሥ
19. የኦሪት ዘሌዋውያን ትርጓሜ
20. በልሳኖች መናገር
21. በጌታ በኢየሱስ ስም የሚሰበሰቡ ክርስቲያኖች /በኦሮምኛ/
22. ኢየሱስ ብቸኛውና እውነተኛው ተስፋችን
23. የራእይ መጽሐፍ ትርጓሜ


## አድራሻ

ለእውነት ቃል አገልግሎት
ፖ. ሣ. ቁጥር 14787
አዲስ አበባ

## ስልክ ቁጥሮች

011-655-8500
011-850-7084
0911-763721
0911-772186


ለ ____________________